# ትንቢተ ዘካርያስ

## ጥናት አንድ - ጠቅላላ መግቢያ

### መጽናኛ

ይህች ዓለም ተስፋ በሚያስቆርጡንና ጌታ እንድንሠራው የሚፈልግብንን ነገር እንዳንሠራ በሚያግዱን ነገሮች የተሞላች ናት። ተስፋ በምንቆርጥበት ወቅትም የእግዚአብሔር በረከቶች ያመልጡናል።

ተስፋ ስንቆርጥ ዓይናችንን ከእግዚአብሔር ላይ አንስተን በአካባቢያችን ያሉትን ሁኔታዎች እንመለከታለን። እነዚህም ሁኔታዎች አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን ነገር እንድንዘነጋ ያደርጉናል። ተስፋ መቁረጦች ከውጭ ይመጡ ይሆናል፥ ይሁን እንጂ ይበልጡን ጊዜ ግን የሚነሱት ከውስጣችን ነው።

እግዚአብሔር ብዙ መጽናኛዎችን እንደሚያዘጋጅልን አትዘንጉ። እነዚህ ነገሮች እንድሚያስፈልጉን እግዚአብሔር ያውቃል። መጽናኛዎች ሁለት ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱም:- ወቅታዊ ችግሮቻችንን የሚያቃልሉንና ዕምነታችንን የምናጸናበትን መሠረት የሚጥሉልን ናቸው።

ከገንዘብ፣ ከዕውቀት፣ ከብርታትና ወዘተ ይልቅ ብዙ መጽናኛ ያስፈልገናል። ትንቢተ ዘካርያስ ባጠቃላይ በዚህ የተሞላ ነው።

### መሠረታዊ ነጥቦች

ዘካርያስ ይህንን መጽሐፍ ሲጽፍ በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር። የሚናገራቸው ነገሮች ከሞላ ጎደል የሚመለከተው በዚህች ከተማ ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለምናገኛቸው ሰዎች በመጽሐፈ እዝራ በተለያዩ ምዕራፎች እናነባለን።

ይሁን እንጂ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አይሁድም ወደ ኢየሩሳሌም ገና አልተመለሱም። ያልተመለሱት ሰዎች በተለያዩ የፋርስ ግዛቶች ውስጥ በመኖር ላይ ነበሩ። ዘካርያስ የሚጽፈው በፋርስና በይሁዳ ለነበሩት ጭምር ነው።

ወደ ይሁዳ የተመለሱት ሰዎችችመምጣት የጀመሩት በ536 ዓክልበ ነው። የአመጣጣቸው ሁኔታ ዝርዝር ታሪክ በዕዝ. 1-6 ውስጥ ቀርቧል። እነዚህ ሰዎች ወደ ይሁዳ ከተመለሱ በኋላ ምንም ነገር ሳይሠሩ ለ16 ዓመታት ኖረዋል። ቤተ መቅደሱን መልሶ የመገንባቱ ሥራ ጨርሶ አልተጀመረም። አሁንም የፍርስራሽ ክምር ሲሆን የሕዝቡም ኑሮ በረከት እንደተለየው ነው።

ተስፋቸውን ሊቆርጡ የቻሉበት አቢይ ምክንያት ድርብ ነው።

1/ ከውጭ በኩል ውጊያ ነበረባቸው። ሰማርያውያን፣ አሞራውያንና ሌሎቹም የኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ነዋሪዎች አጥቅተዋቸው ነበር።

2/ እንዲሁም በውስጣቸው ተስፋ ማስቀረት ስለነበር ጨርሶ ተዳክመው ነው፣ እዝ.3፡3 እና 4፡1-5ን አንብቡ። ምናልባት በፋርስ ነዋሪ የነበሩት አይሁድም ሥቃይ ከዚህ የተለየ አይመስልም።

ስለዚህ እግዚአብሔር መልእክቱን በይሁዳና በፋርስ ለነበሩት አይሁድ እንዲያስተላልፍ ዘካርያስን ይጠቀምበታል።

## ማብራሪያ

መጽሐፉ ቁልጭ ባለ ሁኔታ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል። በምዕ. 1-6 ውስጥ ስምንት ራእዮች ይገኛሉ። በምዕ. 7-14 ውስጥ ስምንት ምክሮች እናገኛለን። እነዚህ ራእዮችና ምክሮች የተለያዩ ሰዎችን ልዩ ልዩ ጉድለቶች የሚያስወግዱ አድርገን ብንመለከታቸው ስህተት ላይሆንብን ይችላል። በኢሳይያስ መጽሐፍም ውስጥ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሁኔታ እናገኛለን። ኢሳ. 1-39 የተፃፈው ለአንድ ቡድን ሲሆን 40-66 ደግሞ ለሌላ ቡድን ነው። የእነዚህ ሁለት መጻሕፍት የማናቸውም ልዩ ልዩ ክፍሎች የተጻፉት በተለያዩ ሰዎች ነው ብለን እንድናስብ የሚያደርገን ምንም ምክንያት የለንም።

ትንቢተ ዘካርያስ በአበይት ትምህርቶች ተከፋፍሎ የተቀመጠ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ የብዙ መጻሕፍት ሁኔታ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል፥ ለምሳሌ፡-የአሞፅ ራእዮች የሰፈሩት በአንድ ሥፍራ ነው። ዘካርያስ በይሁዳ ያገለገለው ለምን ያህል ዘመን እንደሆነ አናውቅም፥ ስለዚህ እነዚህ ራእዮችና ምክሮችም የተሰጡት በጣም በሚራራቁ ጊዜያት ሊሆኑ ይችላሉ። በዘካርያስ ዘመን የይሁዳ ሕዝባዊ መሪ ዘሩባቤል ነበር። እዝራ የመጣው ከ80 ዓመታት በኋላ ነበር።

ባጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ ሁሉ የትንቢቱ አቢይ ትምህርት ተመሳሳይ ነው። መጽሐፉን በምናነብበት በማንኛውም ወቅት ይህ አቢይ ትምህርት እያንዳንዱን የመጽሐፉን ክፍል እንደሚቆጣጠር መዘንጋት አያሻንም። በይሁዳና በፋርስ የነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ መሠረታዊ ችግሮች የተለያዩ ነበሩ። ሕዝቡ መሥራት የሚገባቸውን ነገር ሳያውቁ የቀሩ ሳይሆን ተስፋ ቆርጠው ነበር። የራእዮቹና የምክሮቹ የሁለቱም ዓላማ የይሁዳንና የፋርስን ነዋሪዎች ማጽናናት ነበር።

ሁለቱ የመጽሐፉ ክፍሎች ይዘታቸው ጭራሽ የተለያየ ሲሆን በማጽናኛው አቢይ ትምህርት ተያይዘዋል። ምዕ. 1-6 ተጨባጭነት ያላቸውን ራእዮች ሲያቀርብ ምዕ. 7-14 ትንቢትና ምክር ያዘለ ነው። ይሁን እንጂ ሁለቱም ዓይነት ሃሳቦች በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ይገኛሉ። ምዕ. 1-6 መረጃዎችን ያቀፈ ሲሆን ምዕ. 7-14 እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ የሚያደርጋቸውን ነገሮች የተመረኮዙ ምክሮችን ይዟል። ምዕ. 1-6 በወቅታዊ ችግሮች ላይ ሲያተኩር ምዕ. 7-14 እግዚአብሔር ለሕዝቡ ወዳቀዳቸው የረጅም ጊዜ ዕቅዶች በይበልጥ ያመዝናል። ምዕ. 1-6 በተለይ የሚያተኩረው በይሁዳ ነዋሪዎች ላይ ሲመስል ምዕ. 7-14 እስካሁን በፋርስ በሚኖሩት ሰዎች ላይ ሳይሆን አይቀርም።

ቀጥሎ የቀረበው ቻርት የ14ቱን ምዕራፎች ይዘት በሚመለከት አንዳንድ ሐሳብ ይሰጣል። መጽሐፉን ጠቅለል ባለ ሁኔታ ልናየው ከቻልን ምንጊዜም አጠቃላይ ይዘቱን እንድንገነዘብ ይረዳናል።



# ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ምን እንዳቀደልን ማወቅ ያስፈልገናል። ይህንንም ልናውቅ የምንችለው ቃሉን ሰፋ ባለ ሁኔታ ስናጠና ነው። እግዚአብሔር ራሱንና ለሕዝቡ ያለውን ዕቅዶች ገልጧል። መንፈስ ቅዱስ የተገፈውን ቃሉን ውስዶ በአንባብያን ሕይወት ውስጥ በተግባር ይተረጉመዋል። እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጀውን ነገር ማወቅ ግሩም የመጽናናት ምንጭ ነው።

የእግዚአብሔር ሰዎች በይሁዳ፣ በፋርስ ወይም ደግሞ በየትኛውም ሥፍራ ቢሆኑም ምንጊዜም በርካታ ችግሮች ይገጥሟቸዋል። የውስጥም ሆኑ የውጭ ግፊቶች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተስፋ ያስቆርጣሉ። ይህም ተስፋ መቁረጥ ሕዝቡን እግዚአብሔር ካዘጋጀለት ነገር ያርቀዋል።

በእግዚአብሔር አመለካከት ሁኔታዎችን ማየት ስንችል እነዚህ ተስፋ መቁረጦች ይሸነፋሉ። እግዚአብሔር ወደሚያደርገው ነገር ዓይናችንን ስናነሳ ሌሎቹን ድርጊቶች ሁሉ የምናያቸው ለየት ባለ ሁኔታ ነው። ይህ አቢይ ትምህርት በምዕ. 1-6ና በምዕ.7-14ም ውስጥ በጣም ተስተጋብቷል።

# ከሕይወት ጋር የሚዘመዱ ነጥቦች

እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ማወቅ ያሻናል። እግዚአብሔር ይህንን በምስጢር አልያዘውም። ከገለጠው በኋላ አንዳንድ ሰዎች እንዲፅፉት መርቷቸዋል። እግዚአብሔር ምን ሊሠራ እንደሚያቅድ ከቃሉ ልንረዳ እንችላለን። ይህንንም ለማወቅ ቃሉን ማጥናት አለብን። ይኸውም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን መርጠን በማውጣት በተናጥል ሳይሆን ሰፋ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማጥናት ነው። ተስፋ መቁረጥን ለማሸነፍ የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔር ምን እንደሚያቅድ ማወቅ ነው።

ከዚያም ዕቅዶቹን በተግባር ለመተርጎም ፈቃደኛ መሆን አለብን። ምንጊዜም የርሱ ዕቅድ ዓይነተኛ ነገር ነው። ታዛዥ ስንሆንና ራሳችንን በዕቅዶቹ ውስጥ ስንጨምር እንደ እርሱ ፍላጎት ልንሆንና ፈቃዱን ልንፈጽም እንችላለን። ይህ ፈቃደኝነት የሚመጣው ራሳችን ከምንሰጠው ምላሽ ብቻ ነው፥ እርሱ አያስገድደንም።

እግዚአብሔር በሚናገረው ነገር ላይ መደገፍ ያሻናል። ይህም እምነት ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱን አስታውቋል። አሁን እኛ በቃሉ መሠረት እግዚአብሔር የተናገረውን መውሰድና ቃሉን በተግባር መተርጎም አለብን። የእግዚአብሔር ቃል አይሻርም፥ እንዲሁም ስንታመንበት ለሕይወታችን መጽናናትና በረከት ያስገኝልናል።

# የክለሳ ጥያቄዎች

1. ዘካርያስ ባገለገለበት ዘመን ይተነብይ የነበረው ሌላው ነቢይ ማን ነው?

2. የዚህ ዘመን ታሪክ የሚገኘው የት ነው?

3. አብዛኛዎቹ አይሁድ ከፋርስ የተመለሱት መቼ ነው?

4. በዚያ ወቅት ብዙ ሕዝብ አሁንም ከባርነት ሳይላቀቅ ይኖር የነበረው የት ነው?

5. የዘካርያስ አቢይ መልእክት ምንድነው?

6. ዘካርያስና ሐጌ ይናገሩ የነበረው በየትኛው ዘመን ነበር?

7. በ520 ዓክልበ የተፈፀመው አቢይ ነገር ምንድነው?

8. ትንቢተ ዘካርያስ በስንት ክፍሎች ይከፈላል?

9. ሁለቱን የመጽሐፉን ክፍሎች የሚያጠቃልሉት ሁለት ቃላት ምንና ምን ናቸው?

10. በምዕ. 1-6 ውስጥ ስንት ራእዮች እናገኛለን?

# ጥናት ሁለት - ምዕራፍ አንድ

## የእግዚአብሔር ፍፁም የበላይነት

በሰብዓዊ ዓይናችን ልናይ የምንችለው በቅርብ ያለውን ብቻ ነው። በጣም አርቀን ማየት ይሳነናል። ከሚደረጉት ድርጊቶች ባሻገርና በስተኋላም ምን እንዳለ ማየት አንችልም። ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ስለነዚህ ሁኔታዎች የሚናገረውን ነገር ማዳመጥ ያስፈልገናል። ይህንን መገለጥ ካላገኘን ዘወትር በዙሪያችን በሚደረጉት ነገሮች እንሸበራለን።

ከምናያቸው ነገሮች በስተኋላ የሚፈጸሙትን ሁኔታዎች በእርግጥ ሊገልጥልን የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህ ምዕራፍ በሁለት ራእዮቹ አማካይነት በግልፅ ከሚታየው ነገር በስተጀርባ የሚደረገውን ነገር ይገልጽልናል።

የሰዎች ክፉ አድራጎቶች ቁልጭ ብለው ሊታዩን ስለሚችሉ ሰይጣን የበላይ ተቆጣጣሪ ሆኗል ብለን እንሠጋለን። እነዚህ ነገሮች ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ውጪ ናቸው የሚል ሥጋት ያድርብናል። እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች እንዴት አድርጎ ሊጠቀምባቸው እንደሚችል ወይም በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያደርጋቸው ማየት ይሳነናል።

የእግዚአብሔር የበላይነት ቋሚ የሆነ የነቢያት ሁሉ አቢይ ትምህርት ነው። እግዚአብሔር ሁኔታዎችን ሁሉ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያደርግ ነቢያት ደጋግመው ያሳስቡናል። ጠላት ምንም ታላቅ መስሎ ቢታይም እንኳ እግዚአብሔር በቁጥጥሩ ሥር ያደርገዋል።

## መሠረታዊ ነጥቦች

በነዚህ ጥቂት የመጀመሪያ ምዕራፎች ውስጥ ዘካርያስ በተለይ ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ይናገራል። እነዚህ ሰዎች የተለያዩ ጠላቶች ኢላማ ነበሩ፣ ይሁን እንጂ ሁለቱም ራእዮች በየትኛውም ሥፍራ ለሚኖር የእግዚአብሔር ሕዝብ መልእክት አላቸው፣ ለሁላችን የተሰጡ ራእዮች ናቸው። በይሁዳና በፋርስ የሚኖሩትን የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊያጠፉ የተዘጋጁ አሕዛብ ይገኙ ነበር።

ሕዝቡ በይሁዳ ላይ ከ536-520 ዓክልበ ድረስ ለ16 ዓመታት ቆይተዋል፣ ቢሆንም እስካሁን የቤተ መቅደሱን ግንባታ በሚመለከት ይህ ነው የሚባል ሥራ አላከናወኑም። የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ዘወትር ጠላቶቻቸውን ይመለከቱ ስለ ነበር ማንኛውንም ነገር ለመሥራት ይፈሩ ነበር። ቤተ መቅደሱ መልሰው እንዲገነቡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር፣ ይሁን እንጂ ለ16 ዓመታት ያህል ምንም ነገር አልሠሩም። ለጠላቶቻቸው ሲሉ ዓመታትን እንዲሁ አሳልፈዋል።

ሕዝቡም ቤተ መቅደሱን የመገንባት አቅም እንዳጡ ሲመለከቱ እግዚአብሔር የከዳቸው መስሎ ታይቷቸው ነበር። ሕዝ. 40-48 ለእነርሱ የተሰጡ ተከታታይ ትዕዛዞች

መሆናቸውን ቢረዱ ኖሮ ምንም እንዳይሠሩ አቅም እንዳጡ ይገነዘቡ ነበር። ይህም ተስፋ በመቁረጥ ስሜታቸው ላይ አስተዋፅዖ ነበረው።

የመጽሐፉን አበይት ሀሳቦች አጥብቀን ስንይዝ በምሳሌያዊ አገላለፅ የተሞላው አንዳንድ የመጽሐፉ ቋንቋ ምንም ችግር አይፈጥርብንም። አብዛኛው የመጽሐፉ ቋንቋ ሥዕላዊ ስለሆነ የመጽሐፉን አጠቃላይ አቢይ ትምህርት ተመርኩዘን መተርጎም ያስፈልገናል።

የተለያዩ ነቢያት ወይም ይበልጡ ነቢያት ስለወደፊቱ ሁኔታ የተናገሩ ቢሆንም እንኳ የወደፊቱን ሁኔታ ብቻ የሚጠቁሙት ትንቢቶች በጣም ጥቂት ናቸው። በምዕ. 7-14 የሚገኙት ምክሮች ስለ ወደፊቱ ሁኔታ በዛ ያሉ ማመሳከሪያዎችን ቢይዙም እንኳ ወቅታዊ ተግባራዊነት ነበራቸው።

## ማብራሪያ

1፡1-6 መለኮታዊ መገለጥ በአንድ የተወሰነ ዘመን በእውነተኛ ሰዎች ላይ የሚፈጸም ነው፥ ቁ. 1። እዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ዘመን 520 ዓክልበ ነው። የሕዝቡ ዋና ችግር አቋሞቻቸውን የሚመለከት ነው፥ ቁ.2-3። ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ተጋብዘዋል፥ የግብዣው ጥሪ የሚቀጥለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው። ከምርኮ ቀደም ብለው የተፈጸሙት ድርጊቶች በቁ.4-5 ውስጥ በአጭሩ ተገልጸዋል። ሕዝቡ ኢሳይያስን፤ ኤርምያስን፤ ሰፎንያስንና ሌሎቹንም ሰምተው ምላሽ አንሰጥም በማለታቸው 70 ዓመታት በባቢሎን አጥፍተዋል። በባቢሎን በነበሩበት ዘመን ውስጥ ጥቂት ሕዝብ ንሥሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር ተመልሷል። ይህንንም ያደረጉት እግዚአብሔር የፈጸመባቸውን ነገር ትክክለኛነት አምነው በመቀበል ነበር።

እነዚህ አማራጭ መንገዶች ለእያንዳንዱ አማኝ ተሰጥተዋል። ማንኛውም አማኝ ኮብልሎ ሲሄድ እንዲመለስ እግዚአብሔር ጥሪ ማድረጉን ይቀጥላል።

ጥሪውን አልቀበልም ማለት ቅጣት ያስከትላል። ከዚያ በኋላም እንኳ በረከቶቹን እንዲወርሱ እግዚአብሔር ወደ እርሱ እንዲመለሱ ይጠራቸዋል። ንሥሐ መግባታችን የሚታወቀው ከእግዚአብሔር ድርጊቶች ጋር ስንስማማ ነው።

1፡7-12 መልእክቱ ከእግዚአብሔር የቀረበ በመሆኑ ሥልጣን ያለው ነው፥ ቁ.7። ይህም ራእይ ከዘካሪያስ የተገኘ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተላከ ራእይ ነበር። ፈረሱ የአሦራውያን የጦር እንስሳ ነበር። ፈረሱም ቆሞ ነበር፥ ይህም ሥራው መፈጸሙን ይጠቁማል። ለፈረሶቹ የተሰጡት የተለያዩ ቀለማት ልዩ ምክንያት ያላቸው አይመስልም፥ ቁ.8። አራት መሆናቸው በጉልህ ተገልጿል፥ ዘካርያስ የፈረሶችን ትርጉም ለማግኘት መልአኩን ጠይቆ መልስ ያገኛል፥ ቁ.9። እነዚህ ፈረሶች ምድርን ሁሉ ሊቆጣጠሩ ተሰማርተው ነበር፥ አሁን ወሬ አጠናቅረው ተመልሰዋልም ቁ.10። ፈረሶቹም ያገኙትን ነገር ተናግረዋል፥ ሕዝቡም የሚፈሩበት ምንም ምክንያት የለም። እግዚአብሔር ሁሉም በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል፥ ቁ.11። አሁን ሁሉም ነገር ሰላም

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለጥሪው መልስ እንድንሠጥ ይጋብዘናል። ይህንንም ልንሠጣ የምንችለው ቃሉን ስናነብና ስናጠና ብቻ ነው። ቃሉን እስክናጠናና ለመስማት ዝግጁ እስክንሆን ድረስ ድምፁን ልንሰማ አንችልም። ዛሬስ ለእኛ የሚናገረን ምንድነው? የንሥሐ ጥሪ ዕለት በዕለት በተደጋጋሚ ይመጣል።

ዘወትር እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊቀጣ የሚጠቀምባቸው ኃይላት ሁሉን ነገር በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጉ መስሎ ይታያል፥ ቁ.11። በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተጠቀሰውን ሁኔታ ብቻ ተመልከተን ቢሆን ኖሮ ጨርሶ ተስፋ እንቆርጥ ነበር። በቁ.12 ላይ መልአኩ የጠየቀው ጥያቄ እንዲፈጠር ያደረገው ይህ ጥቅስ ነው። እግዚአብሔር በእርሱና በሕዝቡ ላይ በሚነሱት ሰዎች ላይ ምን እንደሚያደርግ አሁንም አልተገለጠም። ባደረጉት ነገር እንደተቀጣ ይነግረናል። ሁሉን ነገር በቁጥጥራችን ሥር አድርገናል ብለው ስለሚያስቡ እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ እንደሆነ ጨርሶ አልተገነዘቡም።

የእግዚአብሔር ምሕረት ሕዝቡ እንዲያደርጉ በሚያስችላቸው ነገር ተገልጿል። እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ስለተመለሰ ኢየሩሳሌም ከተማን ሊገነቡ ይችላሉ። ቤተ መቅደሱን እንደገና ይሠራሉ፥ ቁ. 16-17።

የአራቱ ቀንዶች በዚህ ሥፍራ መጠቀስ ጠላቶች ገና ያልተሸነፉ መሆናቸውን ይጠቁማል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ድል እንደሚያደርጋቸውና እንደሚያሸንፋቸው ለሕዝቡ ያረጋግጥላቸዋል፥ ቁ. 21።

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

እግዚአብሔር ሕዝቡን ጨርሶ አይጥላቸውም። ቅጣት የተቀበሉት ሰዎች እንኳ ንሥሐ ገብተው ወደ እርሱ እንዲመለሱ ተጋብዘዋል። ምን ጊዜም ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚቻልበት መንገድ ይኖራል። ግብዣው ዋጋ የሚኖረው ሕዝቡ ጥሪውን መስማት ሲችሉ ነው። የሚገኘው የትም ይሁን ጥሪው የማይደርሰው የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል አይገኝም።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተስፋ መቁረጥ የሚሰጠው ምላሽ ምሕረቱ ነው። ይህም ምሕረት የሕዝቡን ችግር ሁሉ ሊያቃልል ይችላል። እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ከነገረን ነገር የተነሳ ብቻ ምሕረቱ ምን ያህል እንደሆነ ልናውቅ እንችላለን።

የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ለሕዝቡ ሁሉ የተሰጡ ናቸው፥ እኛም ልንወስዳቸው ይገባል። ቃሉ የእግዚአብሔር ባሕሪይ ነፀብራቅ ስለሆነ ጨርሶ ሊለወጥ አይችልም።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በ520 ዓክልበ የፋርስ ንጉሥ ማን ነበር?

2. የዘካርያስ አያት ማን ነበር?

3. ሕዝቡ ንስሐ የገቡት መቼ ነው?

4. በቀዩ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ማን ነበር?

5. መልአኩ የተመለከታቸው ሌሎች ፈረሶች ስንት ናቸው?

6. የ70ዎቹን ዓመታት ምርኮ የተነበየው የትኛው ነቢይ ነው?

7. እግዚአብሔር አሁን የተቆጣው በማን ላይ ነው? ተቆጥቶ የነበረው በማን ላይ ነው?

8. እግዚአብሔር ከኢየሩሳሌም የተለየው መቼ ነው?

9. «የቀንዶቹ» ትርጉም ምንድነው?

10. ጠራቢዎቹ የሚያደርጉት ነገር ምንድነው?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ይቆጣል?

2. ይሁዳን የቀጣው እግዚአብሔር ወይስ ባቢሎን ነው?

3. እግዚአብሔር ሁሉን እያወቀ ለምን ዓለምን ያስመረምራል?

4. እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን መምረጡ አድልዎ ነው?

5. ዳንኤል ስለቀንዶቹ ምን ይናገራል?

## የቤት ሥራ

1. ምዕራፍ አንድን እንደገና አንብቡት። በምዕራፉ ላይ የተሰጠውን ማስታወሻ አጥኑ። እስካሁን ያልተመለሰላችሁ ጥያቄ ካለ በወረቀት ላይ ጻፉት።

2. በምዕ. 2 ውስጥ አንድ ራእይ ይገኛል፥ ቁ.1-5። የተቀረው የምዕራፉ ክፍል በተስፋ መልእክት የተሞላ ነው። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ሊሠራ ነው። ለሚቀጥለው ዝግጅት ለማድረግ ይህንን ምዕራፍ አንድ ጊዜ አንብቡት።

# ጥናት ሦስት - ምዕራፍ ሁለት

## የእግዚአብሔር ሐሳብ ለሕዝቡ

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት የሆንን አንዳንዴ ራሳችንንና የተሰማራበትን የእግዚአብሔርን ሥራ መጠበቅ እንደሚኖርብን ይሰማናል። ይህ ትክክል የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል፤ ሆኖም አስፈላጊው ነገር እግዚአብሔር ምን ሊሠራ እንደሚያቅድ ማወቅ ነው።

የእግዚአብሔር ዕቅዶች በቃሉ ውስጥ ተገልጠዋል፤ እግዚአብሔር ምን ሊሠራ እንደሚያቅድ ልናውቅ የምንችለው ቃሉን በማጥናት ብቻ ነው። ይህ ልዩ ራእይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚያደርገው ነገር ላይ ያተኩራል።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የማይሰማው መስሎ ይታያል። እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራ ለጊዜው አይገባንም። እግዚአብሔር ዕቅዶቹን ሁሉ በአንድ ጊዜ አይገልጥልንም። ዕቅዶቹን በሚመለከት የሚገለፅልን ነገር ሁሉ እኛን ለማጽናናት የሚረዳ ብቻ ነው።

እርሱ ለእኛ ያዘጋጃቸው እቅዶች ምንጊዜም መልካም ናቸው። እግዚአብሔርን ለማመን ፈቃደኛ ስለማንሆን አልፎ አልፎ ዕቅዶቹን እንፈራቸዋለን። ዕቅዶቹን የሚገልጡት እነዚህ ራእዮች እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚያስብ ግልጽ ማሳሰቢያዎችን ይሰጡናል። እርሱ ለእኛ ያለውን ፍቅርና ጥንቃቄ ይገልጹልናል።

## መሠረታዊ ነጥቦች

እግዚአብሔር ንጉሥ ቂሮስ እንደሚነሳና ፋርስ ባቢሎንን ድል እንደምታደርጋት በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት ተናግሯል፤ ኢሳ.45፡1-8። ባቢሎንም በፋርስ ተሸንፋለች፤ አይሁድም ወደ ገዛ አገራቸው እንዲመለሱ የፈቀደላቸው የፋርስ መንግሥት ነበር። ይህም የመመለሳቸው ሁኔታ የተጀመረው በ536 ዓክልበ በዘሩባቤል መሪነት ነበር።

የዘሩባቤል ስም በትንቢተ ሐጌና በመጽሐፈ እዝራ ውስጥ በብዛት ቢጠቀስም እንኳ በትንቢተ ዘካርያስ ውስጥ የተጠቀሰው በምዕ.4፡6-10 ባለው አንቀጽ ውስጥ ብቻ ነው። ዘካርያስ ትንቢት ይናገር በነበረበት ዘመን ዘሩባቤል በይሁዳ ወረዳ ሕዝባዊ መሪ ነበር።

ሕዝቡን በሚመለከት ሁለት ነገሮች መገንዘብ ያሻናል፡-

1. በፋርስ ይኖሩ የነበሩት ብዙዎቹ አይሁድ ወደ አገራቸው የመመለስ ዕድል ቢያገኙም አልተመለሱም። ወደ ይሁዳ ከመመለስ ይልቅ በፋርስ መኖር መርጠዋል።
2. ወደ ይሁዳ የተመለሱት አይሁድ በታዘዙት መሠረት ቤተ መቅደሱን እንደገና መገንባት አልቻሉም። በዚህ ዘመን የነበረው ትግል ዝርዝር ሁኔታ በእዝ.1-6 ውስጥ ተሰጥቷል።

ነቢዩ ዘካርያስ በይሁዳና በፋርስ ነዋሪዎች ለሆኑት አይሁድ የተናገረው እነዚህን ሁኔታዎች በማስገንዘብ ነበር።

## ማብራሪያ

2፡1-5 በራእዩ ውስጥ የታየው ሰው በቀያሽ ተመስሏል። በአንድ በኩል ከታየ ከተማይቱ በኮረብታ ላይ ስለተመሠረተች መለካት አያስፈልጋትም፥ ቁ.1-2 ይሁን እንጂ በዚህ ሥፍራ «ኢየሩሳሌም» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከተማይቱን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ባጠቃላይ ነው። በዚህ ራእይ ውስጥ ዘካርያስ ሁለት መላእክት ይመለከታል፥ ቁ.3። እነዚህም ነቢዩን እንዲረዱት የተላኩ ነበሩ። መልእክቱ ደግሞ እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም የሰጠው ነው። እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም በጭራሽ አድርጎላቸው የማያውቀውን ነገር ሊያደርግላቸው ነው። በዚያ ዘመን ማለት በ520 ዓክልበ ከተማይቱ ከምላ ጎደል የፍርስራሽ ክምር ነበረች። እግዚአብሔር ሁለት ነገሮችን ቃል ይገባላቸዋል፥ ይኸውም እንደሚባርካቸውና ከተማይቱን እንደሚያስፋፋት ነበር። 1. ከተማይቱ በዙሪያዋ የግንብ አጥር ማጠር እስኪያዳግታት ድረስ በጣም ሰፊ ትሆናለች፥ ቁ.4። 2. እግዚአብሔር ራሱ ከተማይቱን ይጠብቃታል፥ ቁ.5።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያቀዳቸው ዕቅዶች በዚህ ሥፍራ ተገልጧል። እነዚህ ዕቅዶች ግለሰቦችንና ቤተ ክርስቲያንን ያቅፋሉ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የወደፊት ዕድል በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ መሆኑን ያረጋግጡልናል። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ልንረዳው ባንችልም እንኳ እርሱ እንደሚያውቅ አረጋግጠን ልንቀመጥ እንችላለን።

2፡6-13 አይሁድን የበተነው እግዚአብሔር ራሱ እንጂ አሦር ወይም ባቢሎን አይደሉም። አይሁድ መገንዘብ ያዳገታቸው ይህንን ነገር መረዳት ነበር። አሁን የተቀሩት ሕዝብ ከባቢሎን እንዲሸሹ ጥሪ ያደርግላቸዋል፥ ቁ.6-7። ይህ ራእይ ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ብቻ የተሰጠ አለመሆኑን እነዚህ ጥቅሶች ይገልጹልናል። የእነርሱ ደህንነት የእርሱም እንደሆነ ጌታ ያሳስባቸዋል፥ ቁ.8። የምርኮው ዘመን አብቅቷል፥ አሁን እግዚአብሔር በፋርስ ላይ ሊፈርድ ነው። በዚያን ዘመን አሦርና ባቢሎን ቀደም ብሎ ድራሻቸው ጠፍቷል።

እግዚአብሔር ከዘሩባቤል ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ላልተመለሱት ሰዎች አንድ ጊዜ እንደገና ጥሪ ያደርግላቸዋል። የፋርስ ነዋሪዎች ከከተማይቱ ሁኔታ ይልቅ እርሱን እንዲመለከቱ ይጋብዛቸዋል።

እግዚአብሔር እስራኤልንና ይሁዳን የወረሩትን አሕዛብ በማጥፋት ኃይሉን ሊገልፅ ነው። ከነዚህም መካከል ሁለቱ ታላላቅ አሕዛብ አሦርና ባቢሎን ቀደም ብሎ ተደምስሰዋል። ይህም የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳይ ሲሆን ነቢዩ ዘካርያስም ደግሞ በእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ያረጋግጣል፥ ቁ.9። የኢየሩሳሌም ሕዝብ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ተነግሯቸዋል። እግዚአብሔርም ራሱ በከተማይቱ ውስጥ ሊኖር ይመለሳል። ከዚህ የተነሳ ሕዝቡ ሊደሰቱ ይገባል፥ ቁ.10።

ጠላቶች ለምሳሌ:- ፋርስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሥራ እንቅስቃሴ ልትገታ ጨርሶ አይቻላትም። አሁን የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ይሁዳ ለመመለስ ነፃ ናቸው።

ሕዝቡ በቁ.10 ላይ በተሰጣቸው ምክር መሠረት ምላሽ ሲሰጡ በቁ.11-12 ላይ የተጠቀሱት ውጤቶች ይታያሉ። ሌሎች አሕዛብ መጥተው የእግዚአብሔር ሕዝብ አባላት ይሆናሉ። በዚህ ጊዜ ሁለት ነገሮች ይፈጸማሉ። 1. እግዚአብሔር እንደገና በከተማይቱ ውስጥ ሊኖር ይመለሳል፥ ቁ.11። 2. ዘካርያስ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን ሕዝቡ ይገነዘባሉ፥ ቁ.11። ይህም ሲፈጸም እግዚአብሔር ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን እንደገና የራሱ ልዩ ሐብት አድርጎ ይቆጥራቸዋል፥ ቁ.12።

እግዚአብሔር ከሚያደርገው ነገር የተነሳ ሕዝቡ ዝም እንዲሉና እንዲያስተውሉ ይነገራቸዋል። እግዚአብሔር ከተማይቱን መልሶ የራሱ ንብረት ሊያደርጋት በመንገድ ላይ ነው፥ ቁ.13።

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሕብረት ልዩ ዕቅዶች አሉት። በዚህ ክፍል ኢየሩሳሌም የሚለው ስም የተጻፈው ቤተ መቅደሱን ለመጠቆም ነው። ልዩ በሆነ መንገድ ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔርን መኖር ታመለክታለች። እግዚአብሔር ከዚህ ባልተለየ ሁኔታ በሌሎች ሥፍራዎችም ይኖር ነበር፥ ይሁን እንጂ የእርሱ በኢየሩሳሌም ውስጥ መኖር ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ በጉልህ ይታይ ነበር። በዚያ ሥፍራ መኖሩም በራሱና በሕዝቡ የሥራ እንቅስቃሴዎች ተገልጦ ነበር።

ቂሮስ በ538 ዓክልበ በዙፋን ላይ ከተቀመጠ ጀምሮ አይሁድ ወደ ይሁዳ የመመለስ ነፃነት ነበራቸው። ወደ ይሁዳ የተመለሱትና በፋርስ የቀሩትም አይሁድ ችግሮች ነበሩአቸው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቡ በባቢሎን ወይም በፋርስ እንዲኖሩ አይፈልግም። እግዚአብሔር ወደ ባቢሎን እንዲሄዱ አስገድዷቸው ነበር፥ እንዲመለሱ ግን ማስገደድ አይፈልግም። መንገድ ከፍቶላቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ጋብዟቸዋል።

ጥሪ የተደረገላቸው ብዙ የተለያዩ ነገሮችን እንዲያደርጉ ነው። ይኸውም:- «እንዲሸሹ፥» ቁ. 6-77 «የደስታ መዝሙር እንዲዘምሩ፥» ቁ. 10፤ እንዲሁም «ዝም እንዲሉ» ነበር፥ ቁ.13። እግዚአብሔር ከሞላ ጎደል ሥራውን የሚሠራው በሰዎች አማካይነት ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር ላዘዛቸው ትዕዛዛት ምላሽ ሲሰጡ እርሱ ያቀደላቸውን በረከቶች ይወርሳሉ።

## መሠረታዊ ነጥቦች

እግዚአብሔር ሕዝቡን ከሚፈሩአቸው ጠላቶቻቸው ሊጠብቃቸው በዙሪያቸው «የእሳት ቅጥር» እንደሚሆን ቃል ገብቶአል፥ ቁ.5። 2ኛ ነገ. 6፡8-17ን አንብቡ። የእግዚአብሔር በመካከላቸው መኖርና የኃይሉ መገለጥ የሕዝቡን ምላሽ የተመረኮዘ ነው። እግዚአብሔር ለኛም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የተስፋ ቃል ገብቶልናል፥ ማቴ.

16-18። ይህ የተስፋ ቃል አጠቃላይ እንጂ ለግለሰብ ብቻ የተሰጠ አይደለም። ይህ ልዩ የተስፋ ቃል ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች የተሰጠ ነው፡ ይሁንና ለፋርስ ነዋሪዎችም ተመሳሳይ የተስፋ ቃል ተሰጥቷቸዋል፡ ቁ. 8።

ብዙ ክርስቲያኖች በ «ባቢሎን» ና በ «ኢየሩሳሌም» በሁለቱም ሥፍራዎች ሊኖሩ ይሞክራሉ። የሁለቱንም አገሮች ምርጥ ምርጥ ነገሮች ሊያገኙ የሚችሉ ይመስላቸዋል። «ባቢሎን» የዓለም ምሳሌ ናት፣ 1ኛ ዮሐ. 2፡15-17። ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር በረከት መገኛ ሥፍራ ናት፣ ይኸውም እግዚአብሔር የሚኖርባት ክልል ናት፣ ቁ. 12-13 «ባቢሎን» ምንጊዜም የባርነት ሥፍራ ናት። ማንኛውም የእግዚአብሔር ቤተሰብ በዚያ ሥፍራ መኖር አያሻውም።

እግዚአብሔር የገባልን የተስፋ ቃሎች አሁንም ተፈጽመው ያላለቁ ቢሆንም እንኳ ስለእነርሱ እንድንዘምር ተነግሮናል። የእግዚአብሔር ቃል በጭራሽ አይለወጥም። የተፈጸሙትና ያልተፈጸሙት የተስፋ ቃሎች ዋጋቸው እኩል ነው። እግዚአብሔር ወደ እኛ እንደሚቀርብ የገባልን የተስፋ ቃል ለእያንዳንዳችን የታላቅ መጽናናት ምንጭ ሊሆንልን ይገባል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. መለኪያውን በትር በእጁ የያዘው ማን ነው?
2. ይህ ሰው ምን ሊለካ ነበር?
3. እንዳይለካ የተከለከለው ለምንድነው?
4. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማን የሚጠብቃት ማን ነው?
5. በከተማይቱ ውስጥ የሚታየው ነገር ምንድነው?
6. ሕዝቡ እንዲመለሱ የተመከሩት ከየት ነው?
7. ቁ. 9 የሚያመለክተው ማንን ነው?
8. ሕዝቡ መደሰት ያለባቸው ለምንድነው?
9. ቁ. 9 ና 11 የሚመሳሰሉት በምን መንገድ ነው?
10. ሕዝቡ ዝም እንዲሉ የታዘዙት ለምንድነው?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የኢየሩሳሌም ከተማ ምሳሌያዊ ትርጉም ምንድነው?
2. እግዚአብሔር በቁ. 5 ላይ የሰፈረውን የተስፋ ቃል ለሕዝቡ የሰጠው ለምን ይመስላችኋል?
3. ሕዝቡ ባቢሎንን መተው ያለባቸው ለምንድነው?
4. በምዕ. 2ውስጥ ስንት የተስፋ ቃል ልታገኙ ትችላላችሁ?

5. ምዕ. 2 የተገፈው ለየትኛው ቡድን ሕዝብ ነበር?

## የቤት ሥራ

የሚቀላችሁን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ተጠቅማችሁ ምዕ. 2ን ደጋግማችሁ አንብቡት። ከዚህ ቀደም ብሎ የተሰጠውን ማስታወሻ አንብቡ። ያላችሁን ጥያቄ ጽፋችሁ መልስ ፈልጉላቸው።

ምዕ. 3ን በጥንቃቄ አንብቡ። ሊቀ ካህናቱ የሕዝቡ ተወካይ መሆኑን አትዘንጋ። ከዚህ አንፃር ያለውን የርሱን ተግባር አጥኑ።

## ጥናት አራት - ምዕራፍ ሦስት

## መለኮታዊ ይቅርታ

በክርስትና ትምህርት ውስጥ ምናልባት እጅግ ታላቅ የሆነው ምስጢር መለኮታዊ ይቅርታ ነው። መለኮታዊ ይቅርታን ልንለማመድ እንችላለን፣ ይሁን እንጂ በጭራሽ በከፊል እንኳ ልንገልፀው አንችልም። ሰው እያወቀ የእግዚአብሔርን ትዕዛዞች ጥሷል፥ ሆኖም ያጣውን ሥፍራ መልሶ ለማግኘት ሰው ብቻውን ሊያደርገው የሚችለው ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ቀስቃሽ እርምጃ ካልወሰደ ሰው እንዲሁ «ተቅበዝባዥ»። ሆኖ ይቀራል፣ ዘፍ. 4፡14።

ሰው ይህን የመሰለ አቅም ማነስ ቢኖርበትም እንኳ ማድረግ የሚያሻው የመጨረሻው ትንሽ ነገር የእግዚአብሔር ይቅርታ ያስፈልገኛል ብሎ ማመን ነው። ለራሴ ምንም ነገር ላደርግ አልችልም የሚለውን ነገር መስማት ይጠላል። ሰው ይህንን ይቅርታ ፈልጎ ማግኘት ባይችልም እግዚአብሔር የመጀመሪያውን እርምጃ ስለተራመደ የሚያስፈልገውን ይቅርታ አዘጋጅቶለታል።

ይህ ይቅርታ ቀላል የሆነ ሕጋዊ ፍርድ ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ለዋጭ ኃይል ነው። ይህም ይቅርታ የሚቀበሉትን ሰዎች ሕይወት ይለውጣል። ሰው ሊያደርገው የሚችለው ነገር ቢኖር እጆቹን ዘርግቶ እግዚአብሔር የሚሰጠውን መለኮታዊ ይቅርታ መቀበል ብቻ ነው፥ 2ኛ ቆር. 5፡17።

## መሠረታዊ ነጥቦች

ይህ በመጽሐፉ ውስጥ አራተኛው ራእይ ነው። ራእይ አንድ ፈረሶች፤ ራእይ ሁለት - ቀንዶች ሲሆኑ ራእይ ሦስት ከተማ ነበር። የእግዚአብሔር መልእክተኞች በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ላይ ያጠናቀሩትን የተሟላ ዘገባ አቅርበዋል። ጠላቶች በመጨረሻ ላይ ይደመሰሳሉ። ከተማይቱ ትሰፋለች፥ ጥበቃም ይደረግላታል። ራእይ አራት - ሊቀ ካህናቱ ነው። ይህ ኢያሱ የተባለው ሊቀ ካህናት የሙሴ አገልጋይ ከነበረው የነዌ ልጅ ኢያሱ ጋር በጭራሽ አይገናኝም።

በዘሌ. 21፡16-23 የተሰጠው ገደብ ካላገደው በቀር ሊቀ ካህናት የሚመረጠው ከቀዓት ቤተሰብ ብቻ ነበር። ይህ ቀዓት የተባለው ሰው የአልዓዛርን ቤተሰብ የሚወክል በኩር ነበር። ይህንን ሰው እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንዲሠራ ሾሞት ነበር። የዚህ ሰው ተግባር ወቅታዊ ጥቅምና ምሳሌያዊ ትርጉም ነበረው።

የክህነትን ልብሶችንና በተጨማሪ አሪምና ቱሚም ይለብስ የነበረው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር፥ ዘጸ. 28፡36-43። እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሥራውና የግንኙነቱ ምልክት ነበሩ። በሥርየት ቀን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚፈቅድለት ሰው እርሱ ብቻ ነበር፥ ዘሌ. 16።

በመጀመሪያው ቃል ኪዳን ውስጥ ሊቀ ካህናቱና ተወካዮቹ ሥርየት አብሣሪዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ተግባራቸውን ያከናውኑ የነበረው እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት በሰጣቸው መመሪያዎች መሠረት ብቻ ነበር።

## ማብራሪያ

3፡1-5 ኢያሱ የሊቀ ክህነትን አገልግሎትና ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ይወክላል። ሰይጣን ከሳሽና የተባበረ የክፋት ኃይል ነው፥ ቁ. 1። «የጌታ መልዓክ» ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይወክል አይቀርም። ሰይጣን ኃጢአታቸው ወደ እግዚአብሔር መቅደስ መግባት የከለከላቸውን ሰዎች የመክሰስ መብት አለው፥ ራእ. 12፡10። ለምሳሌ ሕዝ. 8 ከምርኮው በፊት በ 586 ዓክልበ ገደማ ሕዝቡ ምን ዓይነት ኃጢአተኛ እንደነበር ይገልፃል። በሰይጣን ላይ የፍርድ ቃሎች ተነግረዋል፥ ቁ. 2። እግዚአብሔር ኢያሱን ሳያነፃው በፊት እንኳ ከእሳት ይኸውም ከባቢሎን «ነጥቆ አውጥቶታል።»

በራእይ ውስጥ የሚታዩት ሦስት አካሎች፡- ሊቀ ካህናቱ ኢያሱ፤ ሰይጣንና የጌታም መልአክ ነበሩ። ሰይጣን ድል ተመትቶ ሊቀ ካህናቱ ነፃ ይወጣና የሚያምር ልብስ ይለብሳል።

ሊቀ ካህናቱ የለበሰው አዲሱ ልብስ የመንፃቱ ምልክት ነው። ኃጢአቱ ተወስዶለት ንፁሕ ሆኗል። ይህም የመለኮታዊ ይቅርታ ምሳሌ ነው፥ ቁ. 3-4። አሁን አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለው።

ባጠቃላይ ሦስት ነገሮች ተፈጽመዋል፡- 1. ሰይጣን ተገስጿል። 2. የኢያሱ ርኩሰት ከእርሱ ተወስዷል፤ 3. እንዲሁም አዲስና ንፁህ ልብስ ተሰጥቶታል፥ ቁ. 5።

አሁንም ሊቀ ካህናቱ ሕዝቡን በኢየሩሳሌም ሊያገለግል ተዘጋጅቷል። ከ586-536 ዓክልበ ለ70 ዓመታት ያህል ምንም ቤተ መቅደስና የክህነት አገልግሎት አልነበረም። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ወደ ዙፋኑ መቅረቢያው መንገድ አሁን በአዲስ መልክ መመስረቱን ይጠቁማል።

3፡6-10 ሥራው እንደሚባረክለት መልአኩ ለኢያሱ ቃል ይገባለታል። ኢያሱ መታዘዝና ሥፍራውን መሥራት ይጠበቅበታል። ኢያሱ ይህንን ሲሠራ ሁለት የተስፋ ቃሎች ተሰጥቶታል፡- 1 ሥራው አይቋረጥም፥ 2. እንዲሁም የፀሎት አገልግሎቱ ይሰምርለታል፥ ቁ. 6-7። ይህም ቀደም ባሉት ጥቅሶች ውስጥ የተፈጸመው ነገር ቀጥተኛ ውጤት ነው።

ይህ የሊቀ ክህነት አገልግሎት እግዚአብሔር ወደፊት የሚያደርገው ነገር ምልክትም ነው። የሊቀ ካህናቱና የሌሎቹም ካህናት አገልግሎት የታላቁን ሊቀ ካህናት የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሥራ ይጠቁማል። «ቁጥቋጦ» የተሰኘው ስሙ በሰው ደረጃ መገኘቱን ያመለክታል፥ ኢሳ. 4፡2፥ 11፡1፥ ኤር. 23፥ 5 ና 33፡15። ኢየሱስ ክርስቶስ ብሉይ ኪዳን ሊያመለክተው ያቀደው የመጨረሻ ከፍተኛ ግብ ነው፥ ዮሐ. 15ን ተመልከቱ።

«ሰባት ዓይኖች ያሉት ድንጋይ» አንድ ምስክር ብቻ መኖሩና አንድ ድንጋይ ብርቱ መሆኑን ያሳያል፤ «ሰባት ዓይኖች» ምስክሩ ሁሉን የሚያውቅና ፍጹም መሆኑን ይጠቁማሉ። በድንጋዩ ላይ ምን እንደተቀረፀበት አልተነገረንም። ምናልባት «እግዚአብሔር ይቅር ባዩ» የሚል ይሆናል። ይህ ሙሉ ይቅርታ የተከናወነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት ነበር። የዚህም ይቅርታ ውጤት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሕብረት መፈጠሩና ቋሳዊ በረከትም ጭምር ነው፤ ቁ2 9-10።

የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎት ከብዙ አንፃሮች እግዚአብሔር ወደፊት የሚሠራውን ነገር ይጠቁማሉ።

## ማጠቃለያ

በምሳሌው ውስጥ ሰይጣን ስለተጨመረበት የክፋቱ አስከፊነት በጉልህ ታይቷል። ኢያሱንና ቀጥሎም ሕዝቡን ባጠቃላይ ይከሳቸዋል። ሊቀ ካህናቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ሁኔታ ለመሸፋፈን ምንም ጥረት አልተደረገም። እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚገኝበትን ትክክለኛ ሁኔታ አይሸፋፍንም። ይህ ዕውነተኛ የሆነ ነገር የተፍረጠረጠው ግልጽ በሆነ መንገድ ነው። ይህም ይቅርታ የሚታይና የማይታይ ጎኖች እንዳሉት ይጠቁመናል።

ለካህኑ የተደረገው መንፃት ፍጹም ነበር፤ ማለትም የካህኑ ኃጢአቶችና የሕዝቡም ጭምር ሙሉ በሙሉ ተወግደዋል። በዘሌ. 16 ውስጥ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገር እንመለከታለን። ይህንን የመሰለ ሙሉ ይቅርታ የማግኘት ሐሳብ የብሉይ ኪዳን ልዩ አስተዋፅዖ ነው፤ መዝ. 51።

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን መሠረት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው ነገር ከሞላ ጎደል ሁሉም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ጨረፍ ተደርጎ ተገልጧል። «ቁጥቋጦው» ና «ድንጋዩ» የክርስቶስን ፍፁም ሥራ ያመለክታሉ። ብሉይ ኪዳንን በአዲስ ኪዳን ፋና ማንበብ ያስፈልገናል እንጂ የተገላቢጦሽ ሊሆን አይገባም። ሁለቱም ክፍሎች እርስ በርስ ፍንጭ ይሰጣጣሉ።

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

ሰይጣን ዘወትር የንፅህናችንን መጓደል ያሳስበናል። ያገኘነው ይቅርታ ፍፁም ለመሆኑ ዋስትና ማግኘት የሚያስፈልገን ለዚህ ነው። ይህንን ይቅርታ ከመቀበላችን <u>በፊት</u> የነበረንን ሁኔታ ሮሜ 1-3 ያስገነዝበናል። ሮሜ 4-5 ክርስቶስ <u>ያደረገልንን</u> ነገር ይነግረናል። አሁን በክርስቶስ ውስጥ ያለንን ሁኔታ ደግሞ ሮሜ 6-7 ያሳስበናል። በማንኛውም ወቅት ይህንን መሰል የሰይጣን ክስ ሲመጣብን ያገኘነው ይቅርታ ፍፁም መሆኑና ሰይጣንም ይቅርታ በተደረገላቸው ሰዎች ላይ ምንም ዓይነት ክስ ማቅረቡን ሊቀጥል እንደማይችል ልናረጋግጥ እንችላለን።

በ1ኛ ዮሐ. 1፡9 ላይ የሚገኘውን የመሳሰሉ የተስፋ ቃሎችን አጥብቀን መያዝ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ኃጢአት የሚያደርጉትን ሰዎች ይቅር ሊል እንደሚፈልግ እነዚህ ጥቅሶች ያረጋግጡልናል። የይቅርታ ልምምድ ኃይለኛና በተለወጠ ጠባይ ላይ

ሊገለጥ ቢችልም የዋስትናችን መሠረት አይደለም። ጽኑ መሠረታችን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

እግዚአብሔር የሚሰጠን ይቅርታ ፍፁም ነው። የሠራናቸው ኃጢአቶች አንድም ሳይቀር ተደምስሰዋል። እግዚአብሔር ኃጢአቶቻችንን ይቅር የሚለው በከፊል ወይም በገደብ አይደለም። እግዚአብሔር በሚያደርግልን ይቅርታ ውስጥ አንድም እንኳ የሰው አስተዋፅኦ የለበትም። ይህም እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች የሰጠው ስጦታ ነው፥ እኛ የሚያሻን መቀበል ብቻ ነው።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በእግዚአብሔር መልዓክ ፊት የቆመው ማን ነው?
2. ከኢያሱ ጎን የቆመውስ?
3. የኢያሱ ደጎንነት የተመሰለው በምን መንገድ ነበር?
4. ኢያሱ የለበሰው ምን ዓይነት ልብስ ነበር?
5. ይህ ልብስ የምን ምሳሌ ነው?
6. ለኢያሱ ተሰጥቶት የነበረው ምንድነው?
7. ተሰሚ እንዲሆን ኢያሱ ምን ማድረግ ነበረበት?
8. «ቁጥቋጦው» የሚያመለክተው ማንን ነው?
9. የቁጥር ሰባት ትርጉም ምንድነው?
10. የይቅርታ ውጤት ምንድነው?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሰይጣን እንዲቀርብ የፈቀደው ለምንድነው?
2. ኢያሱ አዲስ ልብስ ሊያገኝ የቻለው እንዴት ነው?
3. የእግዚአብሔር መልአክ ምን አደረገ?
4. ኢያሱ ይቅር ከተባለ በኋላ ምን ሠራ?
5. ቁ. 8-10 የሚያመለክቱት የትኛውን ዘመን ነው?

## የቤት ሥራ

1. ምዕ. 3 ን በጥንቃቄ አንብባችሁ የሚያጋጥሟችሁን ጥያቄዎች ሁሉ ፃፏቸው። የሰጣችሁን ማስታወሻ ካነበባችሁ በኋላ የራሳችሁን አስተያየት ጨምሩበት።
2. አምስተኛው ራእይ የሚገኘው በዘካ 4፡፡-5 ና 10-14 ውስጥ ነው። በቁ. 6-10 ውስጥ እግዚአብሔር ለዘሩባቤል የሰጠውን ልዩ የተስፋ ቃል እናገኛለን። ምዕራፉን በሙሉ በጥንቃቄ አንብቡት።

## ጥናት አምስት - ምዕራፍ አራት

## መለኮታዊ መሰናዶ

የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ለዚያ የሚያስፈልግ ብቃት ከእግዝዝአብሔር ማግኘት አለብን። ይህንን ብቃት ካላገኘን ልንሠራ የምንችለው የራሳችንን ሥራ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሥራውን እንድንሠራ ከጠራን ለዚያ ሥራ የሚያስፈልጉትንም ነገሮች ሁሉ ደግሞ አዘጋጅቶ ያቀርብልናል። እግዚአብሔር ጠርቶን ሲያበቃ ውሱንና ጨርሶ ብቃት በሌላቸው የአቅም ምንጮቻችን ላይ እንድንደገፍ አይተወንም።

ሳዖል የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲመራ ተጠርቶ ነበር፥ ሆኖም እምቢተኛ ስለነበር እግዚአብሔር በዳዊት ተክቶታል። ይሁን እንጂ ሳዖል የራሱን የአቅም ምንጮች በመጠቀም ሥራውን ሊቀጥል ተፍጨርጭሯል። ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር በሥራው ላይ በረከት አይታይበትም።

እግዚአብሔር ሁኑ ባለን ሥፍራ ላይ መገኘት ብቻ ሳይሆን ያለማቋረጥ የእርሱን ኃይሎች ማግኘት አለብን። እነዚህ ኃይሎች በተደጋጋሚ የምናገኛቸው ናቸው እንጂ አንዴ ለዘላለም የሚሰጡን ነገሮች አይደሉም። እነዚህ ነገሮች የተሰጡት ለዘለቄታው እንዲያድጉ ተደርገው ነው። ሰጪው እግዚአብሔር ሲሆን እኛ ደግሞ ተቀባዮች ነን።

## መሠረታዊ ነጥቦች

ይህ ምዕራፍ አምስተኛውን ራእይ አቅፏል። የመጀመሪያው ራእይ ስለ ፈረሶች፤ ሁለተኛው ቀንዶችን የሚያመለክት፤ ሦስተኛው በከተማይቱ ላይ የሚያተኩር ሲሆን አራተኛው ከሊቀ ካህናቱ ጋር የተያያዘ ነበር። አምስተኛው መቅረዙን የሚመለከት ይሆናል። የአምስቱም ራእዮች መሠረታዊ ትርጉም አንድ ነው። ሁሉም ለመሪዎችና ለሕዝቡ ባጠቃላይ መጽናናት እንዲሰጡ የታቀዱ ናቸው።

ኢያሱ ወደ ይሁዳ የተመለሰ የሕዝቡ መንፈሳዊ መሪ ሊቀ ካህናት ነው። ዘሩባቤል የይሁዳ ሕዝባዊ አስተዳዳሪ ነበር። እነዚህ ሁለት ሰዎች እግዚአብሔር ሾሞ ሳስቀመጣቸው ሥራ የሚያገለግል የእግዚአብሔር ኃይል ያስፈልጋቸው ነበር። ይህ ራእይ በታየበት ዘመን ሕዝቡ ከ536-520 ድረስ ለ16 ዓመታት በይሁዳ ነበሩ።

ለ16 ዓመታት እነዚህ ሁለት ሰዎች ማለት ኢያሱና ዘሩባቤል መሥራት የቻሉት ነገር እዚህ ግባ አይባልም። ከዚህም የተነሳ ሕዝቡም ወደ ገዛ እርሻዎቻቸው ተመልሰዋል። ጎረቤት አገሮቻቸው ኃይማኖታቸውን እንዲከተሉ ፈተና ሆነውባቸው ነበር ሕዝቡም የራሳቸውን ደካማነት በኢያሱና በዘሩባቤል አሳብበዋል። ይህም ራዕይ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እንደሚያዘጋጅላቸው ለመሪዎቹና ለሕዝቡ ያረጋግጥላቸዋል።

# ማብራሪያ

4፤1-7 ይህ ልዩ ራእይ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ዘካርያስ በጉልህ አሳይቷል፥ ቁ. 1። አንባቢውን ለመጥቀም ሲል ዘካርያስ መቅረዙ ምን እንደሚመስል ገልጿል፥ ቁ. 2-4። መቅረዙ 49 ፈትሎች ነበሩት። ሰባቱ የመቅረዙ ቅርንጫፎች እያንዳንዳቸው ሰባት ሰባት ፈትሎች በድምሩ 49 ፈትሎች ነበሩአቸው። ይህም ፍፁም መሰናዶ መኖሩን ያመለክታል፥ ቁ. 2። በግራና በቀኝ የወይራ ዛፍ ይገኝ ነበር፥ ቁ. 3። ማብራሪያው ወረድ ብሎ ተሰጥቷል።

መልአኩና ዘካርያስ ጥያቄ ይጠያየቃሉ፥ ቁ. 4-5። ከዚያም መልአኩ ለዘሩባቤል መልእክት እንዲያስተላልፍለት ተነግሮታል። ይህ የራእዩ መለኮታዊ አተረጓጎም ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዘሩባቤልን ለድል ያበቃዋል፥ ቁ. 6። መንፈስ ቅዱስ ሁለት ነገሮች እንዲሆኑ ያደርጋል፡- 1. እንደ ተራራ ትልቅ የሆኑ ችግሮች እንኳ ይደመሰሳሉ፥ 2. እንዲሁም ዘሩባቤል የተሰጠውን ሥራ ለመፈጸም የሚያስችል አቅም ያገኛል። ሕዝቡም ደግሞ በደስታ ይሞላሉ።

ይህም ራእዩ ባጠቃላይ በሁለቱ ሰዎች ሥራ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስለመኖሩ እንደሚናገር ይጠቁመናል። እግዚአብሔር በቁ. 6 ላይ በተስፋ የሰጠው ድል በቁ. 2-4 ራእይ ተረጋግጧል።

4፡8-10 ይህ ለዘሩባቤል የተሰጠው ሁለተኛው መልእክት ነው። ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን አሠርቶ ሲጨርስ ሕዝቡ ዘካርያስ ነቢይ መሆኑን ያውቃሉ፥ ሐጌ. 2፤18 ን ተመልከቱ። ከእግዚአብሔር የተላክሁ ነኝ ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ይህ እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጠው ምንድነው? እግዚአብሔር ለዘሩባቤልና ለሕዝቡ ማረጋገጫ ሰጥቷቸዋል። እግዚአብሔር በዘሩባቤል አማካይነት ካደረገው ነገር የተነሳ የሕዝቡ ሐዘን ወደ ደስታ ይለወጣል፥ ቁ. 10።

እግዚአብሔር እንዲያገለግሉት የመረጣቸውን ሰዎች ይመለከታል፥ ይናገራል፥ የተስፋ ቃሎችን ይሰጣል፥ እንዲሁም ያበረታል። እርሱ በሚሰጣቸው የኃይል ምንጮች በሚጠቀሙበት ወቅት ሥራቸው እንደሚቃናላቸው ያረጋግጥላቸዋል።

4፡11-13 ቀጥሎ መልአኩ በቁ. 2-4 ውስጥ የተሰጠውን ራእይ ትርጉም ለዘካርያስ ይተረጉምለታል። ሰባቱ መብራቶች «ሰባቱ የእግዚአብሔር ዓይኖች» ተብለዋል፥ ቁ. 2። መቅረዙ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባበረ ምስክርነት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ምስክርነት ፍሬዎች «የእግዚአብሔር ዐይኖች» ናቸው። የሰባቱ ቧንቧዎች ትርጉም አልተሰጠም፥ ቁ. 2።

ከዚያም ዘካርያስ የሁለቱን የወይራ ዛፎች ትርጉም ይጠይቃል፥ ቁ. 11። ቀጥሎም ስለ ሁለቱ የወይራ ቅርንጫፎች ይጠይቃል፥ ቁ. 12። ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለቱ ቧንቧዎች በዚህ ሥፍራ ተጠቅሰዋል። የወይራ ዘይት ከዛፎቹ ወደ ወርቁ መቅረዝ ውስጥ ይፈሳል፥ ቁ. 12። በቁ. 11-12 ውስጥ የተጠቀሱት ሁለት ነገሮች ትርጉም በቁ. 14 ላይ ተሰጥቷል። እነዚህ ሁለት ነገሮች ኢያሱንና ዘሩባቤልን ይወክላሉ። ስለ እነዚህ ሰዎች

ሁለት ነገሮች ተነግረዋል፤ ይኸውም የተመረጡና የተቀቡ መሆናቸው ነው። እግዚአብሔር «የምድር ሁሉ ጌታ» ተብሎ ተጠርቷል።

## ማጠቃለያ

በእግዚአብሔር፥ በአገልጋዩና በሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት በቁ. 1-3 ራእይ ውስጥ ግልጽ ተደርጓል። ይህም የተደረገው የዘሩባቤልን ሐሳብ ለመሰብሰብና በመካከል ያለውን ግንኙነት በግልፅ ለማሳየት ነው። ከዚያም ዘሩባቤል ድርብ የተሰፋ ቃል ተሰጥቶታል። ይህም ሊሆን የሚችለው በእግዚአብሔር መሰናዶ ሳቢያ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር በዘሩባቤልና በኢያሱ አማካይነት ምን ሊያደርግ እንደሚችል ሕዝቡ ያያሉ። ይህም ሕዝቡን ማጽናኛ መንገድ ነው። የሥራ እንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ውጤት ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ማድረግ ነው።

ወደ ይሁዳ የተመለሱት ሰዎች በመመለሳችን ስህተት ሰርተናል የሚል ስሜት ተሰምቷቸው ነበር። ገና ያልተመለሱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በፋርስ ይኖሩ ነበር። በሁለቱም ሥፍራዎች የሚኖሩት ሰዎች በኢያሱና በዘሩባቤል ላይ የነበራቸውን እምነት አጥተዋል። የራእዩ ጠቅላላ ፍቺ ቁ. 14 ላይ ተሰጥቷል። ሁለቱን ሰዎች «የመረጣቸውና የቀባቸው» «የምድር ሁሉ ጌታ ነው።»

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

ለእግዚአብሔር ስትሰሩ የሚሰማችሁ ልዩ ስሜት ምንድን ነው? እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ለተለያየ ሥራ ይጠራናል። ሁላችን የሚኖረን ኃላፊነት የተለያየ ነው። እግዚአብሔር ቁሳዊና መንፈሳዊ ችግሮቻችንን ሁሉ እንደሚያቃልልን ይህ ራእይ ይጠቁመናል፥ ማቴ. 6፡33 ና ፊልጵ. 4፡19። እግዚአብሔር ጉድለታቸውን ሁሉ ሊሞላ ስለሚችል ሥራቸውን ሊሠምር ይችላል።

የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ምን ጊዜም ዋጋ አላቸው። የእግዚአብሔርንም ባሕርይ ያንፀባርቃሉ፥ የራሳችን እንዲሆኑ ከፈለግን በማንኛውም ጊዜና ዘወትር ልናገኛቸው እንችላለን። ዝርዝር ሁኔታውን ወስደን ተግባራዊ ለማድረግ አሁን ያለንበት ሁኔታ ወሳኝ ነው፥ ይሁን እንጂ አጠቃላይ መመሪያዎቹ በማንኛውም ጊዜና ሥፍራ ዋጋ አላቸው።

እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለአገልጋዮቻቸው የማጽናኛ ቃል ይሰጣል። እግዚአብሔር መሰናዶውንና ጥበቃውን እንዲያረጋግጥላችሁ ምልክት ወይም ራእይ ትፈልጋላችሁ? ተስፋ እንድንቆርጥና እንድንጸከም በጭራሽ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. መቅረዙ የተሠራው ከምንድነው?

2. በመቅረዙ አናት ላይ ምን ነበር?

3. ሰባቱ መብራቶች ስንት ቧንቧዎች ነበሩአቸው?

4. በመቅረዙ ግራና ቀኝ ምን ይገኝ ነበር?

5. ዘሩባቤል የሚሰምርለት እንዴት ነው?

6. የተራሮቹ ትርጉም ምን ምንድነው?

7. የሰባቱ ቧንቧዎች ትርጉም ምንድነው?

8. ዘይቱ የሚፈሰው ከየት ነው?

9. የዛፎቹ ትርጉም ምንድነው?

10. የቅርንጫፎቹስ?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለዘካርያስ ምልክት የሰጠው ለምንድነው?

2. ዘሩባቤል የተሰፋ ቃሎች ያስፈለጉት ለምንድነው?

3. የዘይቱ ትርጉም ምን ይመስላችኋል?

4. ሕዝቡ ስለ ቤተ መቅደሱ ያሰቡት ለምን ነበር?

5. በቁ. 2-4፤ 7ና 14 መካከል ምን ግንኙነት አለ?

## የቤት ሥራ

1. ምዕ. 4ን በጥንቃቄ አንብቡት። የሚያጋጥሟችሁን ጥያቄዎች በሙሉ ፃፏቸው። ይህ ራእይ በእናንተ ሕይወት ውስጥ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል አጥኑ። የምዕራፉን አጠቃላይ መልእክት መረዳታችሁን አስተውሉ።

2. በምዕ. 5 ውስጥ ሁለት ራእዮች ይገኛሉ። ቁ. 1-4 ጥቅልሉ ብራና ሲሆን 5-11 ቅርጫቱ ነው። ይህንን ምዕራፍ በጥሞና አንብባችሁ ለጥናት ተዘጋጁ።

# ጥናት ስድስት - ምዕራፍ አምስት

## ቅድስና

ቅድስና ሰፊ ትርጉም ያለው አጭር ቃል ነው። የቃሉ መሠረታዊ ትርጉም «መለየት» ማለት ነው። «መለየት» አካላዊ ሁኔታን የሚያሳይ ነገር ሳይሆን በኑሮአችን አቅጣጫዎች ሁሉ ላይ መታየት ያለበት አቋም፣ የአኗኗርን ሁኔታና ሕይወትን የሚነካ መሆን አለበት። ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር ሊስማሙ ከማይችሉ ነገሮች ሁሉ መለየት አለብን።

ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል። እነዚህ ክፍሎች እግዚአብሔር ለኃጢአት የሚሰጠውን ምላሽ ይጠቁማሉ። ሰው አውቆ ኃጢአት ቢሠራና ከሠራው ኃጢአት ለመላቀቅ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር እግዚአብሔር ይቀጣዋል። ኃጢአተኛ ኃጢአቱን ለመተው ፈቃደኛ ከሆነ እግዚአብሔር ያስወግድለታል። እነዚህ ሁለት ራእዮች እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአት ላይ ያለውን አቋም ይገልፃሉ።

በምዕ. 3 ላይ እግዚአብሔር የሊቀ ካህናቱን ኃጢአት አስወግዶለታል። በምዕ. 5 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአቶች ላይ ሲያተኩር እንመለከታለን። የሕዝቡን ኃጢአት በሙሉ መደምሰስ የጌታ መልካም ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል ማንም በኃጢአት ቀንበር እንዲሰቃይ አይፈልግም።

## መሠረታዊ ነጥቦች

ይህ ምዕራፍ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን 6ኛ ና 7ኛ ራዕዮች ይዟል። የመጀመሪያው ፈረሶች፣ ሁለተኛው ቀንዶች፣ ሦስተኛው መለኪያው በትር፣ አራተኛው ሊቀ ካህናቱ ሲሆኑ አምስተኛው መቅረዙ ነበር። እያንዳንዱ ራእይ ተመሳሳይ መሠረታዊ ዓላማ እንዳለው ማስታወስ ያስፈልጋል፥ ይኸውም እግዚአብሔር በዘካርያስ አማካይነት ሕዝቡን ማፅናናቱ ነው። ራእዮቹን በሚመለከት ምንም ምስጢር ወይም የተድበሰበሰ ነገር አይገኝም።

በዚህ ክፍል ኃጢአት በቀላሉ የሚታይ ነገር አለመሆኑን እግዚአብሔር ሕዝቡን ያስጠነቅቃል። በግልጽ የሚታየው የኃጢአቱ መንሥኤ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። ይህ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ለኢየሩሳሌምና ለሱሳ ነዋሪ ሕዝብ ነበር። የሕዝቡ ኃጢአት ይወገዳል፥ ይሁን እንጂ አሁንም በፋርስ ይኖሩ ለነበሩት የተሰጣቸው መጽናኛ በጣም ትንሽ ነው።

ራእዮቹ የተሰጡት ወቅታዊ መጽናኛ እንዲሆኑ ብቻ አልነበረም። የማይለወጡ መለኮታዊ ጥቅሞችን የያዙ ናቸው። 6ኛው ራእይ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያለውን አቋም ይገልጻል። በ7ኛው ራእይ ውስጥ እግዚአብሔር ኃጢአትን ከሕዝቡ ማሕበር አውጥቶ ለመጣል ያለውን ፍላጎት እንመለከታለን። ስለዚህ ራእዮቹ ሁለት ተግባራት ይኖራቸዋል።

# ማብራሪያ

5፡1-4 ጥቅልሉ ብራና ሰው ሁሉ ሊያየው በሚችልበት ሥፍራ ላይ ነበር። ከዚያም ነቢዩ ያየውን ነገር እንዲናገር ተጠይቋል፥ ቁ. 1-2። የብራናውን መጠን ለመጥቀስ የተሰጡት ቁጥሮች ጥቅልሉ ብራና ግዙፍ እንደነበር ከመግለፀ በቀር ሌላ ትርጉም ያላቸው አይመስልም። ማንኛውም ሰው ጥቅልሉን መጽሐፍ ሊያየውና ሊያነበው ይችል ነበር። በራሪው ጥቅልል ብራና ከሥፍራ ሥፍራ የሚዘዋወርና ለሁሉም የሚያገለግል መሆኑን ይጠቁማል። የከተማው ነዋሪ ሁሉ ሊያየው የሚችለውን ያህል ሰፊ ሳይሆን አይቀርም። ማንም አላወቅሁም ነበር የሚል ሰበብ ሊሰጥ አይችልም።

ምዕ. 4 በመጽናኛ የተሞላ ሲሆን ይህ ራእይ ደግሞ ማስጠንቀቂያዎችን ብቻ ያቀፈ ነው። ብራናው ከዳር እስከ ዳር እርግማኖችን ወይም ፍርዶችን ይዟል። የተጠቀሱት ሁለት ነገሮች ብቻ ቢሆኑም እንኳ እነርሱ ኃጢአትን ሁሉ እንደሚያጠቃልሉ ለማሳየት ብራናው ከፊትም ከኋላም ተጽፎበታል። ሁለት በጣም የታወቁ ነገሮች ተብራርተዋል፥ ቁ. 3-5።

1. ስርቆት፡- የሌላ ሰው ንብረት የሆነ ማንኛውንም ነገር መውሰድ ማለት ነው። የአንድ ሰው ድርሻ የሆነን ነገር መውሰድ ነው።

2. መዋሸት፡- እውቆ ያልሆነ ነገር መናገር ማለት ነው። ይህም በብዙ መንገዶች ሊደረግ ይችላል። መመዘኛው አድማጩ የሚያገኘው መልእክት ነው።

ኃጢአት የማሕበረሰብ መሠረቶችን ያናጋል። በነዚህ ኃጢአቶች ላይ የተሰጠው ፍርድ በጣም ከበድ ያለው ለዚህ ነው። በዚህ አኳኋን ኃጢአት የሚፈጽሙ የእግዚአብሔር ሰዎች ፍርዱ እንደሚመጣባቸው መረዳት አለባቸው። ኃጢአት ከመሠረቱ አጥፊ ነው። ኃጢአት በታየበት ሥፍራ ሁሉ መሠረቶችን ያናጋል።

5፡5-11 ይህ ራእይ በዘሌ. 16 ውስጥ ከሚገኘው ሐቅ ጋር ይመሳሰላል። በመሠረቱ የራዕዩ ትርጉም ቁ. 6 ላይ ተሰጥቷል። መልአኩ የራእዩን ዓላማና ትርጉም ያብራራል። በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው የመላ ምድሪቱ ኃጢአት ነበር።

በራእዩ ውስጥ አራት ነገሮች ተገልጸውልናል። እነርሱም፡- 1. ከእርሳስ የተሠራው መክሊት ወይም ክዳን፥ 2. የእፍኝ መስፈሪያ፥ 3. በእፍኝ መስፈሪያው ወይም በቅርጫቱ ውስጥ የነበረችው ሴትና 4. የእፍኝ መስፈሪያውን የሚወስዱት መላእክት ነበሩ። መክሊቱ ወይም የእፍኝ መስፈሪያው ክዳን ክፋትን አፍኖ መያዝ የሚያስችል ክብደት ነበረው። የምድሪቱ ኃጢአት በአንዲት ሴት ተመስሏል። የእግዚአብሔር ፍጥረታት የታለሙላቸውን ግቦች ከግቡ እንዳያደርሱ ሰይጣን ያጣምማቸዋል። ሴቲቱን በሚመለከት ማብራሪያ ተሰጥቷል። ኃጢአት በእፍኝ መስፈሪያው ወይም በቅርጫቱ ውስጥ ተጨምሮ ክዳኑ ልክክ ተደርጎ ተከድኖበትና ከዚያም ሁለት ሴቶች ቅርጫቱን ወይም የእፍኝ መስፈሪያውን ወስደውት ነበር።

ዘካርያስ ምክንያቱን ይጠይቃል፥ ቁ. 10። ስለዚህ ሁለት ነገሮች በቁ. 11 ላይ ተነግረዋል። 1. በቁ. 6 የተጠቆመው የምድሪቱ ክፋት ከእርሷ ተወግዷል፥ ይኸውም

ከሕዝቡ መኖሪያ ሥፍራ ተወስዷል፥ ምዕ. 3፡4 ን አመሳክሩ። 2. እንዲሁም ባቢሎን ከፋት የተስፋፋባትና የተመለከባት ማዕከል በመሆን ታውቃለች። በዚህም ምክንያት የጌታ ሕዝብ ከዚያ መሸሽ አለባቸው፥ ሕዝቡ ከባቢሎን እንዲሸሹ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

## ማጠቃለያ

በቁ. 1-4 ውስጥ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆኑ ኃጢአት ብዙ ገጽታዎች አሉት። ሆኖም እነዚህ ሁለቱ ኃጢአትን ሁሉ ይወክላሉ። ለነዚህ ኃጢአቶች የተወሰነው ቅጣት ወደፊት ብቻ የሚፈጸም አይደለም። ይህ ቅጣት የተለመደ ውጤት ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ ምላሽ ነው። የእግዚአብሔር ቅጣት በኃጢአተኛው ላይ የአካልና የኢኮኖሚ ጥፋት ያደርስበታል። ዓላማውም በደለኛው ንስሐ እንዲገባ ነው።

በመጨረሻ መንፃት እንደሚኖር የተነገረው የተስፋ ቃል እርግጠኛ ነው። እግዚአብሔር በግለሰብ ደረጃ ያደረገውን ነገር ሁሉንም በሚያቅፍ ሁኔታ ይፈጽመዋል፥ 3፤5። የመንፃት ሥራ የእግዚአብሔር ሥራ ስለሆነ ለራሱ ልንተውለት ይገባል። አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥራ እኛ ልንሠራው እንፍጨረጨራለን። ይህም ማለት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባላትን መቆጣጠር አያስፈልግም ማለትም አይደለም።

የመጀመሪያው ራእይ በየትም ሥፍራ የሚገኙ የእግዚአብሔር ሰዎችን ይመለከታል። ሁለተኛው ራዕይ በይሁዳ ነዋሪዎች ላይ የተለየ ተግባር አለው። በዚህ ምክንያት የባቢሎን ነዋሪዎች የሆኑት አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ይገባቸዋል፥ 2፡6-7። ይህም የክርስቲያንና የዓለም ምሳሌ ነው።

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚፈጽመው ማንኛውም ኃጢአት ሁሉ በኃጢአተኛው ሕይወት ላይ አጥፊ ውጤት ያስከትላል። ኃጢአት ሊደረግ፤ ሊወደድ፤ ንስሐ ሊገባበትና ከዚያ በኋላ ሊተው የሚችል ነገር አይደለም። ይቅርታ ከተቀበልን በኋላ እንኳ አውቆ የተሠራ ኃጢአት ውጤቶች በቀላሉ እንዲሁ አይወገዱም። ንስሐ የእግዚአብሔርን ሐቀኛ ቅጣት መቀበልንም ይጨምራል።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው የኃጢአት ብርቱ ቀንበር ምርኮኛ ሊሆን አያሻም። የእግዚአብሔር እቅድ በ7ኛው ራእይ ውስጥ ተገልጧል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ይደመስስና ቀስ በቀስ ድሉ በሕይወታችን ውስጥ ይታያል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጥቅልሉ ብራና የት ነበር?

2. የጥቅልሉ ብራና መጠን ምን ያህል ነበር?

3. በተለይ የተወገዙት ሁለት ኃጢአቶች ምንና ምን ነበሩ?

4. ውግዘቱ ወይም እርግማኑ የሚቀመጠው የት ነው?

5. እርግማኑ በዚያ ቤት ላይ ምን ያስከትላል?

6. ቅርጫቱ የምን ምሳሌ ነበር?

7. ክዳኑ ከምን የተሠራ ነበር?

8. በቅርጫቱ ውስጥ ምን ነበረበት?

9. ቅርጫቱ ምን ተደረገ?

10. ቅርጫቱ ወዴት ተወሰደ?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ይረግማል ወይስ ኃጢአትን ይቅር ይላል?

2. ሁለት ኃጢአቶች ብቻ የተገለጡት ለምንድነው?

3. በቁ. 4 ላይ ምን ማረጋገጫ ታያላችሁ?

4. ቁ. 6-8 ከዘሌ. 16 ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

5. ባቢሎን የተመረጠችው ለምን ነበር?

## የቤት ሥራ

ምዕ. 5 ን እንደገና አንብባችሁ ምንም ዓይነት ጥያቄ ሲያጋጥማችሁ በወረቀት ላይ ፃፉት። በምዕራፉ ላይ የተሰጠውንም ማስታወሻ አጥኑ።

ለሚቀጥለው ጥናት ዝግጅት ለማድረግ ምዕራፍ ስድስትን በጥሞና አንብቡ። ይህ ምዕራፍ ከ ቁ. 1-8 ራእይ የያዘ ሲሆን ከ ቁ. 9-15 ባለው ክፍል ውስጥ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን በሚመለከት ልዩ መልእክት አለው።

# ጥናት ሰባት - ምዕራፍ ስድስት

## ክንዋኔ

ላንድ ሥራ ራሳችንን ስናስማራ ሥራው ዋጋ ይኖረዋልና ይሳካል ለማለት ዋስትና እንፈልጋለን። የጀመርነውን ሥራ ልንፈጽም የምንችል መሆናችንን በጭራሽ አለማወቅ ተስፋ የሚያስቆርጥና የሚያሳቅቅ ነው።

እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ እንደሚፈጽም ምን ማረጋገጫ አለን? እስካሁን ድረስ በዘካርያስ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጡት ራእዮች ባጠቃላይ ናቡከደነፆር የደመሰሰውን ቤተ መቅደስ በመገንባት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ይህ ስምንተኛው ራእይ ደግሞ ሥራው እንደሚፈፀም ያረጋግጥልናል።

ይህ ክንዋኔ ከምርኮ የተመለሱት ሰዎች የኢያሱን መንፈሳዊ መሪነት እንዲመሰክሩለት ያደርጋቸዋል። የእግዚአብሔርን ዕቅዶች ለመቀበላቸው ምልክት የሚሆን መታሰቢያ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይቆማል። እግዚአብሔር እንዲያገለግሉት የሰጣቸውን መንገድ ሊጠቀሙበት ይዘጋጃሉ።

## መሠረታዊ ነጥቦች

ጥቂት ሰዎች ከፋርስ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት በ536 ዓክልበ አካባቢ ነበር። በነቢያቱ በሐጌና ዘካርያስ አማካይነት ተጽናንተው ከ16 ዓመታት በኋላ በ520 ዓክልበ ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ቆርጠው ተነስተዋል። እንደገና አገልግሎቶችን ማከናወኛ አድርገው መጠቀም ጀምረዋል። በተጨማሪ መስዋዕቶችንም መሰዋት ጀምረው ነበር።

በ457 ዓክልበ እዝራና በ444 ዓክልበ ነህምያ ደግሞ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ ከተማይቱን በመገንባት ረድተዋል። በቤተ መቅደሱ ሕንፃዎች ላይ ብዙ መሻሻል ተደርጓል፤ ከዚያም በቤተ መቅደሱ ላይ የሚደረገው ለውጥ ቀጥሏል። ሔሮድስ የቤተ መቅደሱን ታላቅ ሕንፃ «ከዓለም አስደናቂ ነገሮች» አንዱ እስኪሆን ድረስ በማስፋትና በማስዋብ 46 ዓመታት ፈጅቷል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሊገለገልበት አልቻለም። በመጨረሻ ላይ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ለቅቆ ወጥቶ በላዩ የፍርድ ትንቢት ተናግሯል። በ70 ዓ.ም. ሮማውያን በቲቶ አዝማችነት ቤተ መቅደሱንና ከተማይቱን ደምስሰዋል። አይሁድም ማመፃቸውን አላቆሙም። በ132 ዓ.ም. ከተማይቱ እንዳለ የአራማውያች ከተማ ሆናለች። አይሁድ ባጠቃላይ ከዚያ ተባርረዋል። ቤተ መቅደሱም በጭራሽ እንደገና አልተገነባም። ባሁኑ ወቅት በጽዮን ተራራ ላይ የእስላም መስጊድ ይገኛል።

## ማብራሪያ

6፡1-8 የሠረገሎቹ ትርጉም ቁ. 5 ላይ ስለተሰጠ ፍቺያቸውን ፍለጋ መሄድ አይኖርብንም። እነዚህ በዓለም ውስጥ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ተመክተው ያዩትን እንዲናገሩ የተሰማሩ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ናቸው። በዘካርያስ ዘመን ከነበሩት

ብረቶች ሁሉ እጅግ ጠንካራ የሚባለው ነሐስ ነበር። ተራሮች የብርታትና የጽናት ምሳሌዎች ነበሩ። በዚህ ሥፍራ በተለይ በሲናና በቀራንዮ ተራሮች ላይ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ምናልባት ሳይወክሉ አይቀሩም። ሠረገሎቹ ወደ ዓለም ሁሉ ስለሚሄዱ አራት ነበሩ፥ አራት ምንጊዜም የዓለምን አንድነት ይጠቁማል።

የፈረሶቹ ቀለማት የተጠቀሱት ለመለያነት ብቻ ሳይሆን አይቀርም። ከምዕ. 1፡8 ጋር ምንም ግንኙነት ያላቸው አይመስልም። ዱሪ! አምባላይ! ቅጥልጣልና መጋላ የተሰኙትን የፈረሶቹን መልኮች ትርጉም ለማግኘት መጣር ምንም ያህል ጥቅም አያስገኝም፥ ቁ. 2-3።

ሠረገሎቹ የተላኩት ለምንድነው? ፋርስ እስከ 333 ዓክልበ ድረስ ስላልተፈረደባት ሠረገሎቹ የተሠማሩት ፍርድ ለማስፈጸም አልነበረም። እነዚህ ሠረገሎች የተሰማሩት በዓለም ላይ ባጠቃላይ ስለሚገኙት የእግዚአብሔር ሰዎች ሁኔታ እንዲሰልሉ ነበር፥ ቁ. 4-5። አንዱ ሠረገላ ወደ ሰሜን ሌላው ወደ ምዕራብ የተቀሩት ሁለቱ ወደ ደቡብ የሄዱ ይመስላል፥ ቁ. 6። ወደ ምስራቅ መሄድ ወደ ባሕር መግባት ይሆን ነበር!

አሁን ነቢዩ ወደ ቁጥር አንድ አጠቃላይ ምሳሌ ይመለሳል። ቁ. 7 ላይ አራቱ ጥንድ ፈረሶች የእግዚአብሔርን ትዕዛዞች ለመታዘዝ ይቸኩሉ ነበር። የኢየሩሣሌምና የፋርስ ነዋሪዎችም ጉጉት እንደዚህ ይሆን! በፋርስ በተለይም በባቢሎን አካባቢ ወደ ኢየሩሣሌም ያልተመለሱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ስለነበሩ የተነገረን እነርሱን የሚመለከት ብቻ ነው።

ቁ. 8 ን ለመተርጎም እንዲረዳን ቁ. 15ን ከእርሱ ጋር ልናያይዘው እንችላለን። ሠረገላው ተግባሩን አከናውኗል፥ ሕዝቡም ከሰሜን ማለት ከፋርስና ከሌሎቹም የዓለም ክፍሎች ጭምር ሊመለሱ ዝግጁ ናቸው። ይህንን ጥቅስ ከ2ኛ ቆሮ. 6፡14-18 ጋር ልናገናዝበው እንችላለን። የእግዚአብሔርን መንፈስ የሚያሳዝኑ ምክንያቶች ሁሉ ተወግደዋል፥ ኢሳ. 63፡10ና ኤፌ. 4፡30። የእግዚአብሔር መንፈስ አሁንም በፋርስ ይኖሩ በነበሩት ምርኮኞች አዲስ ሕይወት አነሳስቷል።

<u>6፡9-15</u> ይህ ክፍለ ምንባብ የያዘው አቢይ ትምህርት ታሪካዊ ሲሆን ከትንቢታዊው ጋር ያደባልቀዋል። በቁ. 10 ላይ ስለተጠቀሱት ሰዎች ምንም የምናውቀው ነገር የለም። ከፋርስ ይዘዋቸው ያመጧቸው ዕቃዎች ትርጉማቸው እንዳይረሳ ቤተ መቅደሱ ከተገነባ በኋላ በውስጡ እንዲቀመጡ ጥቂቶቹን ዕቃዎች መስጠት ነበረባቸው፥ ቁ. 11 ና 14።

ዘውዶቹ በብዙ ቁጥር ቢጠሩም እንኳ ምናልባት በአንድነት ተያይዘው የተሠሩ አንድ ዘውድ ሲሆኑ የመሪነት ምልክት ነበሩ፥ ቁ. 11። በዚህ ሐሳብ መሠረት ዘውዱ ከዚህ በላይ የተሰጡት ሁለት ትርጉሞች ይኖሩታል። 1. ሕዝቡ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር መሪነት ለማስገዛት ፈቃደኝነታቸውን ሲያመለክት 2. የክርስቶስንም የመሢሕነት ተግባር ይጠቁማል። በእሥራኤል ውስጥ ካህን ዘውድ ጭኖ አያውቅም፥ ቁ. 11። የዘሩባቤል ስም በኢያሱ ተለውጦ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚሠነዘረው አስተያየት የጽሑፍ መሠረት የሌለው መላምት ነው። «ቁጥቋጦ» የመሢሁ ስም መሆኑ ገና ድሮውኑ ታውቋል፥ ኢሳ. 4፡2፥ 11፡1፥ ኤር.23፡5 ና 33፡15። በዚህ ጥቅስ ውስጥ

የተጠቀሰው «መቅደስ» የሚለው ቃል ክርስቶስ ሊ.ቀ ካህናትና ንጉሥ የሚሆንባትን ቤተ ክርስቲያንን በትንቢት መልክ ይጠቁማል፥ ኤፌ. 2፡21።

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ዕቅዶች ሁሉ ትብብር ይጠይቃሉ። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቢታዘዙ ተስፋዎቹን ይወርሳሉ፥ ያለበለዚያ ግን እግዚአብሔር እነርሱን ትቶ ለሌሎች ይሰጣል።

## ማጠቃለያ

አሁንም ለመመለስ እምቢተኛ የሆኑትን በሌሎች ሥፍራዎች የሚኖሩትን አይሁድ እንዳልረሳቸው በማሳየት ሠረገሎቹን አሥማርቶ እግዚአብሔር የኢየሩሣሌም ነዋሪዎችን አጽናንቷል፥ ሮሜ 10፡21። የእግዚአብሔር ጥሪ የተደረገው ለማያምኑት ብቻ ሳይሆን ንስሐ ለሚያስፈልጋቸው የእርሱ ቤተ ሰብ ጭምር ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን የካህንና የንጉሥ ሥራ በጭራሽ አብሮ አይሄድም። በዘካርያስ ዘመንም ዘሩባቤልና ኢያሱ የፈፀሟቸው የተለያዩ አገልግሎቶች ናቸው። በአዲሱ ቤተ መቅደስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥና ካህን ይሆናል። ጳውሎስ ይህንን ትምህርት በዕብ. 7 ውስጥ አስፋፍቶታል።

እግዚአብሔር ሕዝቡ በቤተ መቅደሱ ሥራ ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ ይፈልጋል፥ ቁ. 15። ሕዝቡ በፋርስ ሆነው ይህንን ተግባራዊ ሊያደርጉ አይችሉም። ሕዝቡ እርሱ በሚሠራው ሥራ ውስጥ እንዲተባበሩ አሁን ጥሪውን ቀጥሏል።

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

የክርስትና ሕብረት ምንጊዜም በርካታ «የፋርስ ምርኮኞች» ማለት የኮበለሉ ሰዎች ይኖሩታል። እነዚህ ሰዎች በእርግጥ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት ከሆኑ እነርሱን አውጥቶ መጣል በጭራሽ የእግዚአብሔር ሐሳብ አይደለም። እግዚአብሔር በዘካርያስ ዘመን ሠረገሎችን እንዳሠማራ ሁሉ ባሁኑም ዘመን «የፋርስ ምርኮኞች» የሆኑትን የቤተሰቡን አባላት ወደ ራሱ ሊጠራ መልእክተኞቹን ይልካል።

እግዚአብሔር በኑሮአችን ውስጥ ንጉሥና ካህን ሊሆን ይፈልጋል። የሁሉም ጌታ አድርገን አንግሰነዋል? እግዚአብሔር በቁጥጥሩ ሥር ያደረገን ለመሆኑ ምን ምልክት አለን? ቁ. 14። እግዚአብሔር መመሪያና መንፈሳዊ ምክር ይለግሰናል?

በተጨማሪ «የቤተ መቅደሱን ግንባታ» እንድናግዝ ጥሪ ተደርጎልናል፥ ቁ. 15። በቁ. 12 ላይ የተጠቀሰው ቤተ መቅደስ ዓለም አቀፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕብረት ነው። ይሀን እንጂ ሌሎች ሁለት ትርጉሞችም አሉት፡- 1. የግል ሕይወታችን ሲሆን 2. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕብረት ነው። እነዚህን ነገሮች ለመገንባት «ቁጥቋጦ» ተብሎ የተጠራው ሰው አገልግሎት ያሻናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሠረገሎቹ የታዩት የት ነው?
2. ስንት ሠረገሎችና ፈረሶችስ ነበሩ?
3. የሠረገሎቹ ትርጉም ምንድነው?
4. ፈረሶቹ የቸኮሉት ምን ለማድረግ ነው?
5. ወደ ሰሜን የተጓዘው ሠረገላ ምን ፈፀመ?
6. የብርና የወርቅ ሥጦታዎች የተወሰዱት ከየት ነበር?
7. ዘውዱ የተሠራው ለማን ነበር?
8. ካህንና መሪ የሚሆነው ሰው ምን ያደርጋል?
9. ዘውዱ የተቀመጠው የት ነበር? ለምን?
10. የኢየሩሣሌም ቤተ መቅደስ ተመልሶ እንዲገነባ የሚረዳው ማን ነው?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሠረገሎቹን ወደ ዓለም ሁሉ ሲያሠማራቸው ዓላማው ምን ነበር?
2. «ሰሜን» የሚለው ቃል ለአይሁድ ምን ትርጉም ይሰጣቸዋል? ባቢሎንና ፋርስ የተሰኙት ቃላት ለዛሬው ዘመን ክርስቲያኖች የሚሰጡት ምሳሌያዊ ትርጉም ምንድነው?
3. እግዚአብሔር ለምን ተቆጣ? ቁ.8
4. በዚያ ወቅት ይሁዳ የፋርስ ግዛት ክፍለ ሐገርና ነፃ ያልወጣች መንግሥት መሆኗን ስናስታውስ ዘውድ መሠራቱ ምንም ዓመፅ አላስነሳም?
5. ቁ. 15 ያለው የአዲስ ኪዳን ትርጉም ምንድነው?

## የቤት ሥራ

1. ምዕራፍ ስድስትን ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ አንብቡት። የሚኖራችሁን ማንኛውንም ጥያቄ ጻፉ። የምዕራፉን አቢይ ትምህርት መረዳታችሁን አስተውሉ፥ ይህም እያንዳንዱን ጥቅስና ሐረግ ለመተርጎም ይረዳችኋል።
2. ምዕ. 7 ሁለት ክፍሎች አሉት፡-

   ቁ. 1-7 - ከልብ ያልሆነ ጾም

   ቁ. 8-14 - የምርኮው ምክንያት

   ለሚቀጥለው ትምህርት ለመዘጋጀት ምዕራፉን በሙሉ አንብቡት።

## ጥናት ስምንት - ምዕራፍ ሰባት

# ንጽሕና

ከቤተመቅደሱ ጋር ግንኙነት ያለው ነገር ሁሉ ፍፁም ንፁህ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል። ለምሳሌ:- ዘጸ. 25:11፤ 17፤ 24፤ 29፤ 31፤ 36፤ 38፤ 39፤ ወዘተን አንብቡ። ይህ የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ንፁሕ ነገሮችን ብቻ ስለሚቀበል ነው። በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እርሱ ያዘዛቸውን ነገሮች ብቻ መጠቀም ማለት ነው። እግዚአብሔር ስለነገረን ንፁሕ የሆኑ የተወሰኑ ነገሮች ብቻ ናቸው።

የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባላት የሆኑ ሁሉ የእርሱ መኖሪያ ናቸው። ስለዚህ በማንኛውም የኑሮአቸው አቅጣጫ ንጽሕና ይጠበቅባቸዋል፥ ማቴ. 5:8፥ የሐዋ. 20:26፥ ሮሜ 14:20፥ 1ኛ ጢሞ. 1:3 ና 2:22። ንፅህና የሌለው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

ስለዚህ ንፁህ አምልኮ ማለት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ አምልኮ ማለት ነው። ምናልባት ማናቸውም ዓይነት ሌሎች አምልኮዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው ማመን ሊያዳግተን ይችል ይሆናል። በሕይወታችን ውስጥ የንፅህና ጉድለት ካለ የምናቀርበው ነገር ሁሉ የረከሰና እግዚአብሔር የማይቀበለው ነው። ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት በአምልኮ ስንቀርብ በንስሐ ጀምረን የእግዚአብሔርን ይቅርታ በአዲስ መልክ መቀበል ያስፈልገናል።

# መሠረታዊ ነጥቦች

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሥነ-ምግባራዊና ሥርዓታዊ የሆኑት የአምልኮ አቅጣጫዎች ከቃል ኪዳኑ ጋር የተሳሰሩ ነበሩ። ስለዚህ ብሉይ ኪዳንን ስናነብም ሆነ ስናስተምር አንዱ ክፍል ከሌላው መገንጠል ተገቢ አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ ተደጋግሞ የሚፈፀመው ስህተት እግዚአብሔር ከሥነ-ሥርዓት ይልቅ በሥነ ምግባር አምልኮ በጣም የሚደሰት አድርጎ ማሰብ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን በይበልጥ ወደራሱ ለማቅረብ የአምልኮ ሥርዓቶችን ሰጥቷል። በተጨማሪ ሕዝቡ አራሚ ጎረቤቶቻቸውን እንዳይመስሉ ሕጉ አግዷቸዋል። የቤተ መቅደሱ፤ የክህነት አገልግሎቱና የመስዋዕቶቹ ሁሉ ተግባር ይህ ነበር።

ብሉይ ኪዳን በየትኛውም ሥፍራ ሥርዓታዊ አምልኮን ዝቅተኛ አድርጎ አያቀርብም። ሕዝቡ:- 1. የፀጋን ቃል ኪዳን ዘንግተው በሥርዓቶች አማካይነት ብቻ እግዚአብሔር እንዲቀበላቸው ሲጥሩና 2. የሥነ - ምግባር ደንቦችን ቸል ብለው ሥርዓቶችን በማክበር ኃጢአታቸውን ሊሸፋፍኑ ሲሞክሩ ችግሮች ተፈጥረዋል። እነዚህ ሁለት ነገሮች በዘካርያስ ዘመን እንደተፈጠሩ ሁሉ በዛሬውም ዘመን ሊፈጠሩ ይችላሉ።

## ማጠቃለያ

የቤቴል ነዋሪዎች በቤተ መቅደሱ ግንባታ ላይ እንዳልተባበሩ ግልፅ ነው። ስለ ኃጢአታቸው በማልቀስና በመጮህ ላይ በጣም ያተኩሩ ነበር፣ በዚህ ወቅት ይህ ለእነርሱ ምንም ሊጠቅማቸው የማይችል ድርጊት ነበር። በሥርዓታዊ አምልኮአቸው ስለረኩ እግዚአብሔር ላቀረበላቸው ንስሐና ዕድሳት ምላሽ አልሰጡም። የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር በጭራሽ አይቀበለውም ነበር።

ከሙሴ ዘመን ጀምሮ መታዘዝ በረከተን ዕምቢተኝነት ቅጣትን እንደሚያመጡ በቃል ኪዳኑ ውስጥ ለነበሩ ሰዎች እግዚአብሔር ነግሯቸዋል። የቤቴል ልዑካን ይህንን ትምህርት በጭራሽ አልተረዱትም። ተስማሚ የሆነው ምላሽ:- መናዘዝ፤ ንስሐና መታደስ ነበር።

ጥቃቅን የሆኑ ውጫዊ ገጽታዎች ከሥፍራ ሥፍራና ከዘመን ዘመን ይለያዩ እንጂ የእግዚአብሔር ጥያቄዎች አይለወጡም። ምዕ. 7 ዘካርያስ ለፃፈላቸው ሰዎች ትርጉም የሚሰጠን እንደነበር ሁሉ ዛሬም ለኛ ትርጉም ይሰጠናል። እግዚአብሔር አይለወጥም፣ ምዕ. 7 የእግዚአብሔርን ባሕርይ ነፀብራቅ ያሳያል።

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

እግዚአብሔር ምንጊዜም አዳዲስ ነገሮችን ይሠራል። ያለፈው ነገር መናዘዝ፤ ንስሐና ዕድሳት ያስፈልገው ይሆናል። አሮጌ አሠራሮቻችንን ሁሉ ስህተቶችን በፈፀምንባቸው ሥፍራ ላይ ወደ ኋላ በመተው በአዲስ አቋም እንድንነሳና ከእርሱ ጋር እንድንገዛ እግዚአብሔር ለሚያደርግልን ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ መሆን ያሻናል። ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ግልፅ መሆን ይኖርበታል፣ ዕርካታ ሊሰጡን በሚችሉ ሥርዓታዊ አምልኮዎች ላይም መመሥረት የለበትም።

ይሁን እንጂ ስለ እግዚአብሔርና አሠራሮቹ የሚያሳስቡን የአምልኮ ሥርዓቶችን መገንባት ያስፈልገናል። እነዚህን ነገሮች ካልገነባን የግልም ሆነ የሕብረት አምልኮአችን ምሪት የለሽ ይሆናል። አምልኮአችንን ሁሉ ሳናቋርጥ በእግዚአብሔር ቃል ፋና መመርመር ያሻናል። እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ነግሮናል። በእርሱም ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ነገር ብቻ ነው። ከሥነ-ምግባር አንፃር እያደግን ነው? የቤቴል ልዑካን ኑሮአቸውን ለመለወጥ የማይፈቅዱ ነበሩ። ሕይወታችን ለእግዚአብሔር ቃልና ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት ሲሆን እናድጋለን። ኑሮአችን በኑዛዜ፤ በንስሐና በዕድሳት ሕይወት የተመላ ጉዞ ይሆናል። ስለ ንፅህና ያለን አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ሐሳብ እየመሰለ ይሄዳል። የምናደርገው ነገር ሁሉ በይበልጥ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ያገኛል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ይህ መልእክት ለነቢዩ የመጣለት መቼ ነው?

2. ልዑካኑ የመጡት ከየት ነበር?

3. ለዘካርያስ ያቀረቡለት ጥያቄ ምንድነው?

4. ሕዝቡ ከጀመሩባቸው ቀናት አንስቶ ለስንት ዓመታት ጾሙ?

5. እግዚአብሔር የምርኮውን ምክንያት ለሕዝቡ የነገራቸው መቼ ነው? ቁ. 7

6. በመጾም ፈንታ በመካከላቸው ሊያደርጉት የሚገባው ነገር ምን ነበር? ቁ. 9

7. የማህበራዊ ኑሮአቸው ምልክት መሆን የነበረበት ምንድን ነው? ቁ. 10

8. ያደረጓቸው ሦስት ነገሮች ምን ምን ነበሩ? ቁ. 11-12

9. ለፀሎቶቻቸው ያገኙት ምላሽ ምን ነበር? ቁ. 13

10. የዕምቢተኝነት ውጤት ምንድነው?

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የቤቴል ልዑካን ከዘካርያስ እናገኛለን ብለው የጠበቁት ምላሽ ምንድነው?

2. ምዕ. 7 ጾምን ይቃወማል?

3. የቀደሙት ነቢያት የተነበዩት ምን ነበር? ለመልሳችሁ ድጋፍ የሚሆን ጥቅስ ልታቀርቡ ትችላላችሁ?

4. በተሰጣቸው መልስ ውስጥ ስነ ምግባራዊነት ጠበቅ የተደረገው ለምን ነበር?

5. ሕዝቡ በ586 ዓክልበ በምርኮ የተወሰዱት ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

1. ምዕ. 7 ን ለብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ አንብቡት፥ ይህንንም ስታደርጉ መንፈስ ቅዱስ አዳዲስና አስደናቂ ነገሮችን ከውስጡ እንዲያስተምራችሁ ጠይቁ።

2. የምዕ. 8 አቢይ ትምህርት ተሃድሶው። ይህ ምዕራፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሕብረት መታደስን በሚመለከት የተስፋ ቃሎች የተሞላ ነው። ለሚቀጥለው ጥናት ዝግጅት ለማድረግ ምዕራፉን በሙሉ አንብቡት።

# ጥናት ዘጠኝ - ምዕራፍ ስምንት

## ተሃድሶ

ክርስቲያኖች ሁሉ፡- «ነፍሴን መለሳት» የሚለውን ጥቅስ መዝ. 23፡3 ን ያፈቅሩታል። በእንግሊዝኛ፡- «ለፈሰሰ ወተት ማልቀስ አይጠቅምም» የሚል ተረት አለ። ይሁን እንጂ በክርስትና ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር አንድን ነገር እንደፈጠረው አድርጎ መልሶ ሊሠራው እንደሚችል ማረጋገጫ አለን። ይህም ማለት ጥፋቶቻችን ምንም ያህል የበዙና የከፉ ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር መልሶ ሊሠራን፤ ሊያድሰንና ሊያበጀን ይችላል ማለት ነው።

ትንሽም ሆነ ትልቅ ኃጢአት ምንጊዜም ያበላሻል፥ በረከትን ያሳጣል። ኃጢአት እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን በረከቶችና የተስፋ ቃሎች ከናንተ ይወስዳል። እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ውስጥ የገነባውን ነገር ኃጢአት ያፈርሰዋል። ክርስቲያን ኃጢአት ሠርቶ <u>በጭራሽ</u> ከቅጣት ሊያመልጥ አይችልም፥ ይሁንና እንደገና ሊታደስ ይችላል።

እግዚአብሔር ሥጋዊ ሕይወትንና ጤንነትን እንደሚያድስ ሁሉ ኃጢአት በሕይወታችን ውስጥ ያበላሻቸውንና ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር የወሰደብንን ነገሮች ሁሉ ሊያድስ ይችላል፥ 2ኛ ነገ. 8፡1፤ 5፥ ኤር.30፡17፥ መዝ. 51፡10ና 104፡30 እንዲሁም ኤርምያስ በሰቆ. ኤር. 5፡21 ላይ ያቀረበውን ጥያቄ ተመልከቱ።

## መሠረታዊ ነጥቦች

አይሁድ ልዩ ሕዝብ ያደረጋቸውን ባህርይ ሁሉ ምርኮው ከሞላ ጎደል አሳጥቷቸዋል። በ722 ዓክልበ እሥራኤል በአሦራውያን ተወሰዳለች። ይሁዳም በ586 ዓክልበ በባቢሎን ተይዛ ነበር። ከዚያም ቆየት ብሎ ባቢሎን በኋላ የፋርስ ንጉሥ በሆነ በአሻን ንጉሥ በቂሮስ ተይዛለች። ይሁን እንጂ የሕዝቡ የወደፊት ተስፋ የሚገኘው ከምርኮኞቹ መካከል እንደሆነ እግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሰጥቷል፥ ኤር. 24።

አይሁድ አገራቸውን፤ ቤተ መቅደሳቸውን፤ የክህነት አገልግሎታቸውንና የእግዚአብሔርን በመካከላቸው መኖር የሚያረጋግጥላቸውን ታቦታቸውን እንኳ አጥተዋል። ያለቀላቸውና እግዚአብሔርም የተዋቸው መስሏቸው ነበር። በ586 ዓክልበ የተማረከው ትውልድ በባቢሎን ሞቷል ልጆቻቸው በ536 ዓክልበ ገደማ ተመልሰዋል። ለ16 ዓመታት ያህል ብዙ ጭንቀት ውስጥ ስለነበሩ ቤተ መቅደሱን መሥራት ጨርሶ አልጀመሩም።

በ520 ዓክልበ አካባቢ የነበራቸው ተስፋ ምንድነው? እግዚአብሔር ባለፉት 16 ዓመታት ውስጥ ምንም ያላደረገላቸው መስሎ ታይቷቸዋል። አሁንስ ለምን እንደዚያ አይሰማቸውም? <u>አሁን</u> እግዚአብሔር እነርሱን መልሶ የሚያድስበት ዘመን መሆኑን እንዴት ሊያምኑ ቻሉ? ይህ ምዕራፍ ብዙ የተስፋ ቃሎችን እንደያዘ አስተውሉ።

እግዚአብሔር አደርጋቸዋለሁ ከሚላቸው ነገሮች ግርጌ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ አስምሩበት።

## ማብራሪያ

8፡1-5 «ወደ ጽዮን ተመልሻለሁ፥» ቁ. 3። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ፍቅር ሊረዳቸው ባቀደው ዕቅድ ውስጥ ተገልጿል። ከተማይቱን ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሳ ያጠፋት እርሱ መሆኑን ቀደም ብለን በጉልህ ተመልክተነዋል። አሁን ደግሞ መልሶ ያቋቁማታል። እርሱም በውስጥዋ ስለሚኖር አስደሳች ሥፍራ ትሆናለች።

8፡6-8 «ሕዝቤን . . . አድነዋለሁ፥ «ቁ. 7። በዚህ ዘመን ገና «በፋርስ» ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ ብዙ የቤተሰቡ አባላት ይገኛሉ። ሁላቸውንም ሊሰበስባቸው ይፈልጋል። ይህ መቼም የማይቻል ነገር መስሎ ሊታይ ይችላል፥ ዕብ. 6፡6 ን ተመልከቱ። ይሁን እንጂ እርሱ ምንም የማይችለው ነገር የለም።

8፡9-13 « . . . ይህን ሁሉ ነገር አወርሳለሁ፥» ቁ. 12። ሕዝቡ አሁንም በፍርሃት ውስጥ እንደነበሩ ቁ. 9 ና 13 ይጠቁሙናል። ራሳቸውን ይጠራጠሩ ነበር። በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ያረፈ ልብ አልነበራቸውም። በ520 ዓክልበ ገደማ በኢየሩሣሌም አካባቢ ይታዩ የነበሩትን ሁኔታዎች ቁ. 10 ያንፀባርቃል። ሆኖም እግዚአብሔር በቸርነቱ የቀደሙትን ዕርግማኖች ወደ በረከትነት ይለውጣቸዋል። በኃጢአታቸው ምክንያት በመጣባቸው መከራና ሥቃይ ፈንታ አዳዲስ የተስፋ ቃሎች ተሰጥተዋቸዋል። እግዚአብሔር የተበላሸውን ነገር ሁሉ ሊያድስና ነጥቋቸው የነበረውንም ነገር ሁሉ ሊመልስላቸው ነው፥ መዝ. 23፡3።

8፡14-17 «በጎነትን አደርግ ዘንድ አስቤአለሁ፥» ቁ. 15። በ722 ና በ586 ዓክልበ እግዚአብሔር ቅድመ አባቶቻቸውን ቀጥቷል። እነዚህ ልጆቻቸውም ከእነርሱ በምንም አይለዩም። ይሁን እንጂ እንደገና ሁሉንም ነገር በአዲስ መልክ እንዲጀምሩ ዕድል ተሰጥቷቸዋል። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው መለኮታዊ ፀጋ ብቻ ነው። እነዚህ በቁ. 16-17 ውስጥ የተሰጡት የተስፋ ቃሎች እንዲሁ የተሰጡ አይደሉም። ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ባሕርይ በሚስማማ አኳኋን ምላሽ ሊሰጡ ይገባል። እግዚአብቤር የማይወዳቸውን እነዚህን ሦስት ነገሮች እንጠላለን? ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።

8፡18-19 « . . . የሐሴትም በዓላት ይሆናል፥» ቁ. 19። አራቱ የጾም በዓላት ወደፊት አይከበሩም። ይህ የለቅሶና የዋይታ ወቅት አይደለም። ጾሞቹ ወደ ግብዣ ይለወጣሉ፥ ይህም የተሃድሶ ወቅት ነው! የተለወጠው የሕዝቡ የአኗኗር ምልክት በእግዚአብሔር ፊት ዕውነተኛ መሆንና እርስ በርስ ሰላም መፍጠር ይሆናል።

8፡20-23 «ብዙ ወገኖችና አህዛብ . . . ይመጣሉ፥» ቁ. 22። የሕይወትና የስነምግባር ተሃድሶው ዓለማቀፍ አገልግሎትን ያስገኛል። እነዚህ ጥቅሶች በዘካርያስ ዘመንና አካባቢ ምንም ዓይነት ፍፃሜ ቢያገኙም የሐዋ. 2 ንም ደግሞ ይጠቁማሉ፥ እንዲሁም ገና ወደፊት የሚፈፀም ነገር ይቀራቸዋል። እነዚህን የመሳሰሉ ጥቅሶች

በሚሰጡን ፋና አማካይነት የብሉይ ኪዳን ነቢያት በመጨረሻ የአሀዛብ መንግሥታት እንደሚሰበሰቡ መመልከታቸውን ማየት እንችላለን።

## ማጠቃለያ

ተሃድሶው ሊጀምር የሚችለው እግዚአብሔር ሲያነሳሳ ብቻ ነው። ጾምና ፀሎት የእግዚአብሔርን ድምፅ እንድንሰማ ሊያዘጋጀን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ኃጢአት ያበላሸውን ነገር ለማደስ በራሳችን ኃይል ምንም ልናደርግ አንችልም። ይህ መቶ በመቶ በእግዚአብሔር ፀጋ ላይ የተደገፈ ነው፤ ሆኖም እግዚአብሔር መልሶ ሊያበጀው የማይችለው ምንም ነገር እንደሌለ በጉልህ መረዳት አለብን። እግዚአብሔር እንዲሠራ ዝግጁ ስንሆን እርሱ ያደርገዋል፤ ቁ. 1-5።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ መፍራት ከሰይጣን ነው። በነቢዩ አማካይነት ለሕዝቡ የተሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ፍርሃታቸውን አጥፍቶላቸዋል፤ ቁ. 9፤ 13 ና 15። ምንጊዜም ሰይጣን፡- «ተሸንፋችኋል» ይለናል። እግዚአብሔር ስለ ተሃድሶ የሰጠንን የተስፋ ቃሎች እንዳንቀበል ተስፋ ሊያስቆርጠን ይፈልጋል። ሕዝቡ የተስፋ ቃሎቹን ለመቀበልና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሲሆኑ ድክመቶቻቸውን ሁሉ ድል ማድረግ የሚያስችል ብርታት እግዚአብሔር ይሰጣቸዋል።

በረከቶቹም እንድንወርሳቸው የተሰጡን ናቸው፤ ቁ. 14-23። የእግዚአብሔር ባሕርይ ስለማይለወጥ ቃሉም በጭራሽ አይለወጥም። በ516 ዓከልበ አካባቢ ይኖር ለነበረው ሕዝብ የተነገረው ነገር ሁሉ በዛሬው ዘመን ላለነውም የሚሰጠው አገልግሎት ልዩነት የለውም። እግዚአብሔር እነዚህን በረከቶች አዟል፤ ታዲያስ ለምን ያመልጡናል? በሙሴ ዘመን የተስፋ ቃሎቹን ባልወረሱት ሰዎች ላይ ምን እንደደረሰ አስታውሱ! ዋነኞቹ ተቀባዮች በሲና ምድረ በዳ ሲሞቱ ሌላ አዲስ ትውልድ የተስፋ ቃሎቹን ወርሷል። ይህ በእኛም ሕይወት እንዲፈጸም ለምን እንፈቅዳለን?

## ከሕይወት ጋር የሚዛመዱ ነጥቦች

እግዚአብሔር ወደ እኛ ሊጠጋ እንዲችል እንቅረበው። መታደስ የማይችል እስኪመስል ድረስ በኃጢአት የተንኮታኮተው የናንተ «ኢየሩሣሌም» ምንድነው? ከምርኮ የተመለሱት አይሁድ የደረሱበት ደረጃ ማለት የእግዚአብሔርን ፍርድ መቀበል ደረጃ ላይ ደርሳችሁ ይሆናል። የናንተ «ኢየሩሣሌም» ከኃጢአት የተነሳ በእግዚአብሔር እንደተደመሰሰ ተረድታችኋል። ይሁንና ያ ነገር አሁንም ፍርስራሽ ሆኖ መቆየት አያሻውም። የተስፋ ቃሎቹን በመቀበል እርሱ ያንኮታኮተውን ነገር መልሶ ሲሠራው ተመልከቱ።

በተለምዶ ተሃድሶን መቀበል ያስፈራናል። ይህም ምንም ጭብጥ የሌለው ሐሳባዊ ስሜት ብቻ እንደሆነ አድርገን ለራሳችን እንናገራለን። የሚቻል መስሎም አይታየንም። ሌላ ዕድል የማይገባን ሰዎች አድርገን ራሳችንን ልንቆጥር እንችል ይሆናል። አምላካችን እግዚአብሔር የማይቻለውም ነገር ሁሉ ጌታ ነው። እኛ ማድረግ የሚሳነንን ነገር እርሱ

ያደርገዋል። ራሳችን የምናወጣውንና የምናወርደውን ሐሳብ ሳይሆን የእርሱን ቃል መቀበል ይገባናል።

እንውረስ ወይስ እንመርምር? እግዚአብሔር ኃጢአት ያፈራረሰውንና አንኮታኩቶ የጣለውን ነገር መልሶ ሊያድሰው እንደሚፈልግ ምዕ. 8 ገልፆልናል። እግዚአብሔር ሕይወታችንን ሊባርክ እየተጠባበቀ ስለሆነ ምንም ነገር ሳናደርግ ለምን እንቀመጣለን? ለተቀረው የሕይወት ዘመናችን የመጀመሪያው ቀን ዛሬ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ተቀብለን በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ እናድርግ!

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ኢየሩሣሌምን ሊረዳ የሚፈልገው ለምንድን ነው? ቁ. 1
2. እግዚአብሔር ወደ ኢየሩሣሌም ሲመለስ በከተማይቱ ውስጥ ምን ይፈጸማል? ቁ. 4-5
3. ገና እንደተበተኑ ለነበሩት ሰዎች ምን ያደርግላቸዋል? ቁ. 7-8
4. በ520 ዓክልበ ገደማ የነበሩት ሰዎች ሁኔታ የሚያሳየው ምልክት ምንድነው? ቁ. 9-10
5. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምን ሊሠራ ነው? ቁ. 11-12
6. እግዚአብሔር ሊባርካቸው ስለሆነ ሕዝቡ ምን ማድረግ ይገባቸዋል? ቁ. 16-17
7. ጾሞቻቸው ምን ይሆናሉ? ቁ. 19
8. ሰዎች ወደ ኢየሩሣሌም የሚመጡት ለምንድነው? ቁ. 20-21
9. ሕዝቡ ወዴት ይመጣሉ? ቁ. 22
10. የሚመጡትስ ሰዎች ብዛት ስንት ነው? ቁ. 23

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በዚህ ክፍል ኢየሩሣሌም የምን ምሳሌ ናት?
2. የዚያ ዘመን ሕዝብ ይፈራ የነበረው ለምንድነው?
3. እግዚአብሔር በሚያድስበት ወቅት ሁሉ የሚያደርጋቸው አንዳንድ ለውጦች ምን ምንድናቸው?
4. እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚሻው ምንድነው?
5. ተሃድሶው የሚነካው ማንን ነው?

# የቤት ሥራ

1. ብዙ ጊዜ ደጋግማችሁ ምዕ. 8 ን አንብቡ። ለእናንተ እንደተጻፈ አድርጋችሁ ማንበብ አትዘንጉ። እግዚአብሔር በዚህ ምዕራፍ አማካይነት የሚናገረኝ ነገር ምንድነው? ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ።

2. የምዕ. 9 አቢይ ትምህርት <u>ነፃነት</u> ነው። ዕውነተኛ ነፃነትን የሚያውቁ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው። ምዕ. 9 ን በማንበብ ለሚቀጥለው ጥናት ዝግጅት መላልሳችሁ አሰላስሉት።